## ኢትዮጵያ ፡ ለምታደርገው ፡ የኢኮኖሚ ፡ ዕድገት ፡ የሚሆን ፡ የአስተዳደር ፡ አቋም ።

ከአይን ፡ ኤስ ፡ ፍሬዘር ።

በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪቃ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ኮሚሲዮን ።

### ምዕራፍ ፡ ፩ ።

### መግቢያ ።

ገና ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ባሉት ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ለዕቅድ ፡ ለማስተባበር ፡ ለሥራ ፡ ማኪያሄጃና ፡ ዕቅዱን ፡ ለማመዛዘን ፡ የሚረዳ ፡ የአስተዳደር ፡ ፈሊጥ ፡ ይሠራል ፡ ተብሎ ፡ የሚጠብቀውን ፡ ዋስትና ፡ ለመስጠት ፡ በጣም ፡ ያዳግታል ። አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ የዕቅዱን ፡ አቀነባበር ፡ ከመለዋወጥ ፡ ይልቅ ፡ የዕቅዱ ፡ ጉዳይ ፡ የሚመለከተውን ፡ ዕቅዱን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውለውን ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ የሥራ ፡ ድርጅትና ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ማሻሻል ፡ የበለጠ ፡ ጥቅም ፡ ሊያስገኝ ፡ ይችላል ። ፕሮፌሰር ፡ ቢ ፡ አርዝናውስኪ ፡[1] እንዳለው ፡ ሁሉ ፡ "ባንዳንድ ፡ አገሮች ፡ ውስጥ ፡ ዕቅድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የማይችልበት ፡ ምክንያት ፡ ውጥኖቹን ፡ (ፕሮጄዎችን) ፡ ያቀረቡት ፡ ክፍሎች ፡ ሥራቸውን ፡ በሚገባ ፡ ስለማይሠሩ ፡ ነው ፤ ወይም ፡ እነዚህ ፡ ክፍሎች ፡ ፈጽመው ፡ ስለሌሉ ፡ ነው ።"

በዚህ ፡ ረገድ ፡ ኢትዮጵያም ፡ ብዙዎቹ ፡ ገና ፡ በመልማት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አገሮች ፡ በሚገኙበት ፡ ሁኔታዎች ፡ ትገኛለች ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጠቅላላ ፡ የልማት ፡ ብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡[2] ካወጡት ፡ ከመጀመሪያዎቹ ፡ የአፍሪቃ ፡ አገሮች ፡ አንዷ ፡ ብትሆንም ፡ ይህ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የቻለው ፡ በቅርብ ፡ ነው ። ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ገና ፡ በመኪያሄድ ፡ ላይ ፡ ይገኛል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ አዲሱን ፡ ብሔራዊ ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ለጊዜው ፡ የወጣው ፡ የአስተዳደር ፡ አቋም ፡ እንከን ፡ እንዳለበት ፡ ባለፈው ፡ የሥራ፡

---

ሚስተር ፡ አያን ፡ ኤስ ፡ ፍሬዘር ፡ ቀድሞ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የፐብሊክ ፡ አድሚንስትሬሽን ፡ እንስቲቲዩት ፡ ዲሬክተር ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪቃ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ኮሚሲዮን ፡ የሕዝብ ፡ አስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ሹም ፡ ናቸው ።

1. ቢ ፡ አርዝናውስኪ ፡ ኮምፕርሄንሲቭ ፡ ፕላኒንግ ፡ ኢን ፡ ሰም ፡ አፍሪካን ፡ ካንትሪስ ፡ (መስከረም ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፤ ገና ፡ ያልታተመ) ።

2. ለሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ (ፕላን) ፡ ዕቅድ ፡ መግቢያ ፡ የሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ የመጀመሪያው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ የመጀመሪያው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጠቅላላ ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፤ መመሪያ ፡ (ፖሊሲ) ፡ ሆኖ ፡ መቅረቡን ፡ ይገልጻል ። ኢትዮጵያ ፡ ለኢኮኖሚና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕድገት ፡ መስፋፋት ፡ ተገቢ ፡ የሆነ ፡ ዕቅድ ፡ ለማውጣት ፡ ከአፍሪቃ ፡ የመጀመሪያዋ ፡ አገር ፡ መሆኗንም ፡ ይኸው ፡ ጽሑፍ ፡ ይገልጻል ። በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የተዘጋጀውን ፡ ሁለተኛውን ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ (፲፱፻፷፫-፲፱፻፷፯ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ) ፡ ገጽ ፡ ፴፫ ፡ ተመልከት ።

ልምድ ፡ ተረድተነዋል ።[3] አፍታ ፡ የማይሰጡ ፡ ችግሮችም ፡ ባጋጠሙ ፡ ቍጥር ፡ አስፈላጊው ፡ መሻሻል ፡ እንዲደረግ ፡ እርምጃ ፡ ተወስዷል ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትም ፡ (ፕላኒንግ ፡ ቦርድ ፡ ኦፊስ) ፡ ብዙ ፡ የለውጥ ፡ ሐሳቦችን ፡ አቅርቦ ፡ ነበር ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ በዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ገና ፡ ብዙ ፡ መሠራት ፡ አለበት ።

በሚኒስቴሮችና ፡ በሌሎች ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ መካከል ፡ ያለውን ፡ መተባበርንና ፡ መግባባትን ፡ በይበልጥ ፡ ማሻሻል ፤ ባለግል ፡ ነጋዴዎችን ፡ የሚያበረታታ ፡ የሚያንቀሳቅስ ፡ የሚመራ ፡ ፖሊሲን ፡ ማውጣት ፤ ዓመታዊውን ፡ ባጀት ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጋር ፡ ማዛመድ ፤ ለማስፈጸም ፡ ኀላፊዎች ፡ ማን ፡ እንደሆኑ ፡ በግልጽ ፡ ዘርዝሮ ፡ መስጠት ፤ እነዚህ ፡ ከነዚህ ፡ የሚዛመዱ ፡ የአስተዳደር ፡ ዘዴ ፡ ለውጦች ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በተፋጠነ ፡ ዘዴ ፡ እንዲከናወን ፡ የሚረዱ ፡ ይመስላል ።

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ የተጠቃለለ ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ ምርመራ ፡ ማድረግ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ዐውቆ ፡ እንደ ፡ አውሮጳ ፡ አቆጣጠር ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ፕሮፌሰር ፡ ቢ ፡ አርዝናውስኪ ፡ ስለ ፡ "ኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ ዕቅድ ፡ አቋሞች" ፤ ሚስተር ፡ ጂ ፡ ኤፍ ፡ ሉባ ፡ ስለ ፡ "ልማት ፡ (ካፒታል) ፡ ባጀት ፡ ማዘጋጀትና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ማዋል" ፤ ጥናት ፡ አድርገው ፡ መግለጫ ፡ እንዲሰጡ ፡ አድርጎ ፡ ነበር ። ሁለቱም ፡ ሰዎች ፡ የሚገኙት ፡ ከተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ የአፍሪቃ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ኮሚሲዮን ፡ (ዩኔካ) ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ በላይ ፡ በተጠቀሱት ፡ መግለጫዎችና ፡ ከነሱ ፡ በተዛመዱ ፡ በፖለቲካና ፡ የአስተዳደር ፡ ጉዳዮችና ፡ ክርክሮች ፡ መሠረት ፡ አንድ ፡ ብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በመጠናት ፡ ላይ ፡ ይገኛል ።

የትእዛዙ ፡ ረቂቅ ፡ "ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አንድ ፡ የተባበረ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር" ፡ እንዲኖር ፡ ያዛል ። በትእዛዙም ፡ የሚከተሉት ፡ ተጠቅሰዋል ።

(፩) የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡

(፪) የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ኮሚቴ ፡

(፫) የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡

(፬) እንደሚከተለው ፡ ሆነው ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ትእዛዝ ፡ በተጨማሪ ፡ የሚቋቋሙ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ድርጅቶች ፤

(ሀ) በየቀጠናው ፡ (በየወሰኑ) ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ ከሚመለከታቸው ፡ ከልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ እንደራሴዎች ፡ ከተውጣጡ ፡ የተቋቋሙ ፡ የቀጠና ፡ የሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ (ኮሚቴዎች) ፤ እያንዳንዱ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በአንድ ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን ፡ ሊቀመንበርነት ፡ ይመራል ።

---

3. ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለልማት ፡ ዕቅድ ፡ ተግባር ፡ መሠረት ፡ የሚሆን ፡ ሕግ ፡ እምብዛም ፡ የለ ። በተለይ ፡ ከዚህ ፡ ጉዳይ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያለው ፡ ሕግ ፡ በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መቋቋም ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ። (ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፲፭ ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፤ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫) ፡ ሆኖም ፡ ለጥቂት ፡ ዓመታት ፡ የምክር ፡ ቤቱ ፡ ተግባር ፡ የሚካሄደው ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በጉባኤው ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍልና ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሆኗል ።

(ለ) የኢኮኖሚ ፡ ልማትና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ከሚመለከታ
ታቸው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚቋቋሙ ፡
የልማት ፡ ድርጅቶች ፡ በየክፍሉ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ፡ ሹም፡ ቍጥጥ
ርና ፡ መሪነት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራን ፡ ያዘጋጃሉ ።

"የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች" ፡ የሚባሉት ፡ "ሁሉም ፡ ሚኒስቴሮች ፡
መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የመንግሥት ፡ ወኪል ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በቻርተር ፡ የተቋ
ቋሙ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ በሙሉም ፡ ሆነ ፡ በከፊል ፡ በመንግሥት፡
ባጀት ፡ የሚካሔዱ ፡ ከማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ወይም ፡ ከኢኮኖሚ ፡ ልማት፡
ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸው ፡ የመንግሥት ፡ የሆኑ ፡ ባለሥልጣን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች፡"
ናቸው ።

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የዕቅድ ፡
ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተግባሮችና ፡ ሥልጣኖች ፡ በሚከተሉት ፡ ምዕራፎች ፡[4] ውስጥ ፡
ይብራራሉ ።

ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ጠቅላላ ፡ ሁኔታ ።

(፩) <u>የግላዊ ፡ ድርጅቶችና ፡ የመንግሥት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተግባር</u> ።

"የኢትዮጵያ ፡ ኢኮኖሚ ፡ የመንግሥት ፡ የግልና ፡ የኅብረት ፡ ሥራ ፡ ድር
ጅቶች ፡ ሁሉ ፡ ተካፋይ ፡ ሊሆኑበት ፡ የሚገባ ፡ ድብልቅ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ነው ። ይህ ፡
ዕቅድ ፡ የመንግሥትና ፡ የግል ፡ የልማት ፡ ሥራዎችን ፡ ማስተባበር ፤ መምራትና ፡
የሁለቱ ፡ ክፍሎች ፡ የልማት ፡ ተግባሮች ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ እንዲደጋገፉ ፡ ማድረግ፡
አለበት ። ከሥራው ፡ ከፍተኛ ፡ የሆነ ፡ መልካም ፡ ውጤት ፡ በማግኘት ፡ ብሔራዊ
ውን ፡ ፍላጎት ፡ ለማርካት ፡ የኢኮኖሚ ፡ ወይም ፡ የሶሺያል ፡ አገልግሎት ፡ ነክ ፡ የ
ሆኑ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውጥኖች ፡ በመንግሥትና ፡ እንዲሁም ፡ በግል ፡ ድርጅቶች ፡ ይከ
ናወናሉ ። እነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ክፍሎች ፡ በአገሪቱ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ውስጥ ፡ እኩል ፡ የሆነ፡
ደረጃን ፡ የያዙ ፡ ስለሆኑ ፡ እርስ ፡ በራሳቸው ፡ ተደጋጋፊዎች ፡ ሲሆኑ ፡ በዚሁ፡ መሠ
ረት ፡ ሁለቱም ፡ ክፍሎች ፡ ለአገሪቱ ፡ ልማት ፡ ማበርከት ፡ ይኖርባቸዋል ።"[5]

በሕዝቡ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ቀጠና ፡ በኩል ፡ የኢትዮጵያ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅ
ድና ፡ በየዓመቱ ፡ የሚወጡት ፡ የሥራ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ሠንጠረዦች ፤ ያለውን ፡ ካፒ
ታል ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ ለማዋልና ፡ መፈጸም ፡ የሚገባቸውን ፡ ውጥኖች ፡ ተቆጣጥሮ፡
ለማከናወን ፡ መመሪያ ፡ እንዲሆኑ ፡ ተገምተዋል ። በግል ፡ ቀጠና ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፤
የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ዓላማ ፡ ለሕዝቡ ፡ የግቡን ፡ በሮች ፡ ማሳየት ፡ ብቻ ፡
ነው ። ይሁን ፡ እንጂ ፤ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፤ ሕዝቡ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ፡
ከታሰበው ፡ ግብ ፡ ለመድረስ ፡ እንዲችል ፡ ማነቃቃትና ፡ ማደፋፈሩን ፡ አይተውም።
ለግቡ ፡ የሚስማሙትን ፡ ውጥኖችና ፡ መዋጮዎች ፡ ሲያደፋፍር ፡ የማይጠቅሙ
ትን ፡ ደግሞ ፡ ያስወግዳል ።

ለሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ሠላሳ ፡ በመቶ ፡ የሚሆነው ፡ ለል
ማት ፡ የሚውለው ፡ ገንዘብ ፡ ከግላዊ ፡ ንብረት ፡ ያዥ ፡ ክፍሎች ፡ እንደሚሆን ፡

4. እታች ፡ ምዕራፍ ፡ ፫-(፪) ፤ (፫) እና ፡ ምዕራፍ ፡ ፬-(፫) ፡ (፬) ፤ (፭) ፡ ተመልከት ።

5. ገጽ ፡ ፴፭ ፡ ተመልከት ።

ይገመታል ። ይኸውም ፡ ከሀገሪቱ ፡ ባጀት ፡ ሌላ ፡ ከሀገር ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙ ፡ የሀብት ፡ ምንጮችና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ ይገኛል ፡ ተብሎ ፡ የታሰበ ፡ ነው ። ከዚሁም ፡ ሒሳብ ፡ ሃያ ፡ ሁለት ፡ በመቶ ፡ የሚሆነው ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የግል ፡ ባለንብረቶች ፡ እንደሚገኝ ፡ ተገምቷል ። ይህንኑ ፡ ለማድረግ ፡ የሀገር ፡ ውስጥን ፡ ሆነ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ግላዊ ፡ ባለሀብቶች ፡ ገንዘባቸውን ፡ (ካፒታላቸውን) ፡ በልማት ፡ ውጥኖች ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉ ፡ ማደፋፈር ፡ ያስፈልጋል ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ዓላማ ፡ (ፖሊሲ) ፡ ግላዊ ፡ ድርጅቶችን ፡ በተለይም ፡ በሌላ ፡ አገሮች ፡ የመንግሥት ፡ ሥራዎች ፡ ተብለው ፡ የሚቆጠሩ ፡ ተግባሮችን ፡ የሚያከናውኑትንና ፡ እንዲሁም ፡ ባንዳንድ ፡ ምክንያት ፡ የግል ፡ ባለሀብቶች ፡ ለመሞከር ፡ የማይደፍሩትን ፡ ሥራ ፡ የሚያካሂዱትን ፡ ለመርዳት ፡ ነው ። የፖስታ ፡ ቴሌግራፍና ፡ ቴሌፎን ፡ ሚኒስቴር ፡ በትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፩/፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡[6] በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የፖስታ ፡ አገልግሎቶችን ፡ ይሰጣል ። በመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ ቍ ፡ ፪፻፲፫/፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡[7] በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን ፡ የኤሌክትሪክ፡መብራትን፡ለማከፋፈል፡“ሞኖፖሊ”፡አለው።የኢትዮጵያ፡ን፡ነ፡መ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ በተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቍ ፡ ፻፴፩/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡[8] መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መ ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ ቦርድ ፡ ማንኛውንም ፡ በንግድ ፡ በኩል ፡ ያለውን ፡ የቴሌኮሙኒኬሽን ፡ አገልግሎት ፡ (በሀገር ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ አገር) ፡ ለመስጠት ፡ “ሞኖፖሊ” ፡ አለው ። የኢትዮጵያ ፡ አኤሮፕላኖች ፡ ማኅበር፡ በኢትዮጵያ፡ አኤሮፕላኖች፡ ማኅበር ፡ ድንጋጌ ፡ በቍጥር ፡ ፺፱/፲፱፻፴፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡[9] በወጣው ፡ የመንግሥት ፡ ማስታወቂያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ማኅበር ፡ ተብሎ ፡ ተቋቁሞአል ። ያዲስ ፡ አበባ ፡ ማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ የውሃ ፡ ክፍል ፡ ለአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተማ ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ውሃ ፡ ያድላል ። በቀሩትም ፡ ከተሞች ፡ የሚገኙ ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ለየከተማቸው ፡ ነዋሪ ፡ ሕዝብ ፡ ውሃን ፡ ለማደል ፡ ኀላፊ ፡ ናቸው ።

ከነዚህ ፡ በተለይ ፡ ሕግ ፡ ወጥቶላቸው ፡ በመንግሥት ፡ ባጀት ፡ ከሚተዳደሩ ፡ ድርጅቶች ፡ ሌላ ፡ የንግድ ፡ ሕግ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥትና ፡ ድርጅቶቹ ፡ የአብዛኞቹ ፡ የአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ አባል ፡ ናቸው ።[10] የዚህም ፡ ዋና ፡ ዓላማ ፡ እንዱስትሪዎች ፡ እንዲስፋፉ ፡ ለማበረታታት ፡ ነው ።

የንግድና ፡ የእንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ የአዲስ ፡ አበባ ፡ ነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የልማት ፡ ባንክና ፡ የቴክኒክ ፡ ድርጅት ፡ ለግል ፡ ንብረት ፡ ያገር፡ ድርጅቶች ፡ ምክርና ፡ ርዳታ ፡ ይሰጣሉ ።[11] ከንግድና ፡ እንዱስትሪ ፡ ሚኒስትር ፡ ሥ

---

6. ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፭) ።

7. የኢትዮጵያ ፡ ኤሌክትሪክ ፡ መብራትና ፡ ኃይል ፡ ባለሥልጣን ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፭) ።

8. የኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መ ፡ ቴሌኮሙኒኬሽን ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፴፩/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፭) ።

9. የኢትዮጵያ ፡ አይሮፕላኖች ፡ ማኅበር ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፴፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፬) ።

10. በ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በተለይ ፡ በወጣ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ቍጥር ፡ ፫ ፡ የታደለና ፡ በዚሁ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በንግድ ፡ ሕግ ፡ አዋጅ ፡ የታወጀ ፤ (አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፻፷፮/፲፱፻፶፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፱ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፫) ።

11. እታች ፡ ምዕራፍ ፡ ፭-(፪) ፡ ተመልከት ።

ራዎች ፡ እንዱ ፡ ንግድን ፡ ማስፋፋትና ፡ እንዱስትሪዎችን ፡ ማበረታታት ፡ ነው ። [12] ሚኒስትሩም ፤ ንግድ ፡ እንዲስፋፋ ፡ የሚረዳውን ፡ የነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤትን ፡ እንዲያቋቁም ፡ ተወስኖ ፡ ነበር ።

የኢትዮጵያ ፡ የልማት ፡ ባንክ ፡ በአዋጅ ፡ ቍ ፡ ፪፲፮/፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ተቋቋመ ። [13] የባንኩም፡ ተግባሮች ፡ የሚከተሉት ፡ ናቸው ።

(፩) በኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የእንዱስትሪና ፡ የእርሻ ፡ ልማት ፡ እንዲስፋፋ ፡ ለመርዳት ።

(፪) በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ገንዘቦች ፡ ጥቅም ፡ በሚሰጡ ፡ ሥራዎች ፡ ላይ ፡ እንዲውሉ ፡ ለማድረግ ፤ ባንኩ ፡ የተቋቋመበትን ፡ ሥራ ፡ ለማከናወን ፡ እንዲችል ፤ ገንዘብ ፡ እንዲያበድርና ፡ ለተበዳሪዎችም ፡ ዋስ ፡ እንዲሆን ፡ "እስቶክ" ፡ እና ፡ "ቦንድ" ፡ አውጥቶ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውልና ፡ እንዲሁም ፡ ገንዘቡን ፡ በንግድ ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውልና ፡ በንግድ ፡ ሥራዎች ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆን ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ።

የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክን ፡ የተካው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ በትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፴/፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በቻርተር ፡ ተመሠረተ ። [14] ይህም ፡ ባንክ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ን ፡ ነ ፡ መ ፡ ባንክ ፡ ነው ፤ የሌሎችም ፡ ባንኮች፡ ሁሉ ፡ የበላይ ፡ ነው ። በተለይም ፡ ገንዘብ ፡ እንዲቀረጽ ፡ እንዲታተምና ፡ እንዲወጣ ፡ ማድረግ ፡ የገንዘብንና ፡ የክሬዲትን ፡ መጠን ፡ መቆጣጠርና ፡ መመጠን ፤ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የኢንተርናሲዮናል ፡ መጠባበቂያ ፡ ሒሳቦችንና ፡ ገንዘቦችን ፡ መምራትና ፡ ማስተዳደር ፤ እነዚሁም ፡ ባንኮች ፡ የሚቋቋሙበትን ፡ ፈቃድ ፡ መስጠትና ፡ ሥራቸውን ፡ መቆጣጠር ፡ ይችላል ። የገንዘብና ፡ የባንክ ፡ ሥራ ፡ ዐዋጅ ፡ ቍ ፡ ፪፻፮/ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ [15] በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ባንክና ፡ ለአዲስ ፡ አበባው ፡ ባንክ፡ ፈቃድ፡ ሰጥቷቸዋል ። በተጨማሪም ፡ "ባንክ ፡ ዲ ፡ ሮማና" ፡ "ባንክ ፡ ናፖሊ" ፡ በቀድሞው ፡ ስምምነት ፡ መሠረት ፡ በኤርትራ ፡ ጠ/ግዛት ፡ ውስጥ ፡ አገልግሎት ፡ በመስጠት ፡ ላይ ፡ ይገኛሉ ።

የኢትዮጵያ ፡ ንግድ ፡ ባንክ ፡ ለአብዛኞቹ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለተቋቋሙት ፡ ለአክሲዮን ፡ ማኅበሮች ፡ የተወሰነ ፡ እስቶክ ፡ ይሰጣቸዋል ። የተወሰኑ ፡ አክሲዮኖች ፡ ብቻ ፡ በኢትዮጵያውያኖች ፡ እንዲገዙ ፡ ሲደረግ ፡ አብዛኞቹ ፡ አክሲዮኖች ፡ በየትኛውም ፡ ዜጋ ፡ ሊገዙ ፡ ይችላሉ ።

## (፪) <u>የልማት ፡ ፖሊሲ ፡ የሚከናወንባቸው ፡ ዘዴዎች ፡ (መሣሪያዎች) ።</u>

ለሕዝቡ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ የሚያስፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ የሚመጣው ፡ ከዓመታዊ ፡ ባጀትና ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ብድርና ፡ ርዳታ ፡ ነው ። የግል ፡ ቀጠናን ፡ ለመቆጣጠር ፡ የታክስ ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ብድርና ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንዛሪ ፡ ደንቦች

---

12. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፩/፲፱፻፴፭ ፡ ተመልከት ።

13. የኢትዮጵያ ፡ የልማት ፡ ባንክ ፡ የተቋቋመበት ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፲፮/፲፱፻፶፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፮) ።

14. የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ቻርተር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፴ ። (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳) ።

15. አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፮ ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፪ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፳) ።

ን ፡ ማውጣት ፡ ያስፈልጋል ። ቴክኒካዊ ፡ ጥናትና ፡ ምርምር ፡ የሚደረገበትንና ፡ ሙያተኞች ፡ የሚሰለጠኑበትን ፡ ሁኔታ ፡ ማቃለል ፤ ንዋይ ፡ ጠቀስ ፡ ያልሆነ ፤ ለሁለቱም ፡ ክፍሎች ፡ የሚረዳ ፡ ዘዴ ፡ ነው ።

በልማት ፡ ላይ ፡ እንዳሉት ፡ አገሮች ፡ ሁሉ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ለጊዜው ፡ ሥራ ፡ ማኪያሄጃ ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ችግር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ይህንን ፡ ችግር ፡ ለማለፍ ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ ለልማት ፡ ማስፋፊያ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የታቀደውን ፡ በጀት ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዳይሠራበት ፡ ያደርገዋል ። የተወሰነ ፡ በጀት ፡ ሳይመደብላቸው ፡ በየሚኒስቴሮቹ ፡ በማብቃቃት ፡ ብቻ ፡ እንዲሠሩ ፡ የሚዘጋጁ ፡ ውጥኖች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ። ገንዘብ ፡ ባጠረ ፡ ጊዜ ፡ በጀት ፡ የሚቀነሰው ፡ አንዳንድ ፡ አስቸኳይ ፡ ያልሆኑትን ፡ ውጥኖች ፡ በመተው ፡ ሳይሆን ፡ ከሁሉም ፡ የበጀት ፡ ክፍል ፡ የተወሰነ ፡ ገንዘብ ፡ በመቀነስ ፡ ነው ።

የልማት ፡ በጀት ፡ እንዴት ፡ እንደሚዘጋጅና ፡ ከልማት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ ጋር ፡ እንዴት ፡ እንደሚቀናጅና ፡ በሥራም ፡ ላይ ፡ ሲውል ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እንደሚሻሻል ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ በሚገኙት ፡ ምዕራፎች ፡ ውስጥ ፡ ይብራራል ።

የውጭ ፡ ሀገር ፡ ርዳታና ፡ ብድር ፡ ከልማት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ ጋር ፡ የተዛመዱ ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ርዳታዎች ፡ ጠንቅ ፡ ሳይኖራቸው ፡ አይቀርም ። እነዚሁንም ፡ በምዕራፍ ፡ ፯ —(፩) እናብራራለን ።

የውጭና ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ በቍ ፡ ፺፩/፲፱፻፶፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ ፡[16] አዲስ ፡ የሚቋቋሙትን ፡ የልማት ፡ ድርጅቶችንና ፡ በርከት ፡ ያለ ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ማዋል ፡ የያዙትን ፡ ድርጅቶች ፡ ከገቢ ፡ ግብር ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸዋል ፤ በተለይም ፡ ለእርሻና ፡ ለእንዱስትሪ ፡ ሥራ ፡ የሚያገለግሉ ፡ የእርሻና ፡ የእንዱስትሪ ፡ መኪናዎች ፡ ከገቢ ፡ ዕቃ ፡ ቀረጥ ፡ ነፃ ፡ ሆነው ፡ እንዲገቡ ፡ ይፈቅዳል ፤ እንዲሁም ፡ በሀገር ፡ ውስጥ ፡ ተሠርተው ፡ ወደውጭ ፡ የሚላኩትን ፡ ዕቃዎችን ፡ ከውጭ ፡ ቀረጥ ፡ ነፃ ፡ ያደርጋቸዋል ። ገንዘባቸውን ፡ (ካፒታላቸውን) ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ያዋሉ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባለሀብቶች ፡ ከዚሁ ፡ ሥራቸው ፡ ያገኙትን ፡ ትርፍ ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ለማስተላለፍና ፡ ሒሳቡን ፡ ባጣራ ፡ ጊዜ ፡ ከዚሁ ፡ የሚገኘውን ፡ የተጣራ ፡ ገንዘብ ፡ ለመውሰድ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ ምንዛሬ ፡ እያስተላለፈ ፤ በተጨማሪም ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ለተገኙት ፡ ብድርና ፡ ወለድ ፡ ዋናውንም ፡ ብድር ፡ ለመክፈያ ፡ የሚሆን ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንዛሬ ፡ ይፈቀዳል ። እንደዚሁም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ዜጎች ፡ ሲቀጠሩና ፡ ዕቃዎች ፡ ሲገዙ ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ምንዛሪ ፡ እንዲተላለፍ ፡ ይፈቀዳል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ከተገለጹት ፡ አንዳንዶቹ ፡ የማበረታቻና ፡ የመሳቢያ ፡ ዘዴዎች ፡ ከአሁን ፡ በፊትም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ድርጅት ፡ በተለይ ፡ ቢፈቀዱም ፡ ቋሚ ፡ ሆነው ፡ በሕግ ፡ መደንገጋቸው ፡ ለወደፊት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ገንዘባቸውን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በሚፈልጉ ፡ ባለሀብቶች ፡ መተማመኛ ፡ ይሆናቸዋል ፡ ተብሎ ፡ ይገመታል ። ያለውም ፡ ሕግ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ወጣ ፡ ውጤቱ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለማወቅ ፡ አይቻልም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ የሕግ ፡ አንቀጾች ፡ ለልማት ፡ የሚውለውን ፡ ግላዊ ፡ ሀብት ፡ ለማግኘት ፡ በጣም ፡ ይረዳሉ ።

ጠቅላላ ፡ የታክስ ፡ አቋምን ፡ ከልማት ፡ ዕቅድ ፡ ጋር ፡ ለማዛመድ ፡ የሚደረገው ፡ ጥረት ፡ አነስተኛ ፡ ነው ። ላጭር ፡ ጊዜ ፡ ግቦች ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ በቅድ

16. ድንጋጌ ፡ ቍጥር ፡ ፺፩ ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፳፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩) ።

ሚያ፡ ለማግኘት፡ የሚደረገው፡ ጥረት፤ ባለፈው፡ ጊዜ፡ ከተሠሩት፡ ሥራዎች፡ ግምትና፡ ከጥንት፡ የገንዘብ፡ አሰባሰብ፡ ጋር፡ ያለው፡ ግንኙነት፡ ላዲስ፡ የልማት፡ ዕቅድ፡ የሚሆኑ፡ ለውጦች፡ በጊዜ፡ እንዳይደረጉ፡ አድርገውታል።

ምንም፡ እንኳን፡ ከግምሩክ፡ ታክስ፡ ነጻ፡ መሆን፡ ጠቅላላ፡ ድጋፍ፡ ቢሰጣቸው፡ በልማት፡ ላይ፡ ያሉ፡ እንዱስትሪዎች፡ ከ"ታሪፍ"፡ ነጻ፡ እንዲሆኑ፡ የተወሰደው፡ እርምጃ፡ የተወሰነ፡ ነው። የታክስ፡ መጠን፡ ምን፡ ያህል፡ እንደ፡ ሆነ፡ ስላልተረጋገጠ፡ የእንዱስትሪዎች፡ እድገት፡ አይፋጠንም። ከባለርስቶች፡ የሚገኘው፡ ታክስ፡ አነስተኛ፡ ከመሆኑም፡ በላይ፡ በመሬት፡ ከመጠቀም፡ የተነሣ፡ ከሚገኘው፡ ትርፍ፡ ገንዘብ፡ ላይ፡ የሚቆረጠውን፡ ታክስ፡ መሰብሰብ፡ አዳጋች፡ ስለ፡ ሆነ፡ ያለው፡ ካፒታል፡ በልማት፡ ዕቅድና፡ በልማት፡ ሠንጠረዥ፡ ላይ፡ ላሉት፡ ነገሮች፡ መዋሉ፡ ቀርቶ፡ ለሌላ፡ ነገሮች፡ እንዲውል፡ ይደረጋል።

ሕዝቡ፡ በባንክ፡ በኩል፡ ገንዘብ፡ እንዲያጠራቅም፡ የሚደረገው፡ ጥረት፡ እምብዛም፡ አስደሳች፡ ውጤት፡ አላስገኘም። ሰው፡ ባንክ፡ ላይ፡ ጥርጣሬ፡ ስላለው፡ የአብዛኛው፡ ሰው፡ ገቢ፡ አፍ፡ ከእጅ፡ በመሆኑ፡ በመገናኛ፡ በኩል፡ ብዙ፡ ችግር፡ ስለአለና፡ ባንኮችም፡ በብዛት፡ ስለሌሉ፡ በባንክ፡ መጠቀም፡ በጣም፡ የተለመደ፡ አይደለም። ይህም፡ በሀገሩ፡ ውስጥ፡ ተጠራቅሞ፡ ለልማት፡ እንዲውል፡ የሚችለውን፡ ካፒታል፡ አሳንሶታል። ለጊዜው፡ የልማት፡ ባንክ፡ ከውጭ፡ አገር፡ እየተበደረ፡ በሀገር፡ ውስጥ፡ ብድር፡ መስጠት፡ ይዟል። ይሁን፡ እንጂ፡ ለእርሻ፡ ውጥኖችና፡ ለእንዱስትሪዎች፡ ልማት፡ የሚያስፈልገው፡ ገንዘብ፡ ከልማት፡ ባንክ፡ እንደ፡ ልብ፡ ሊገኝ፡ አልተቻለም። የልማት፡ ባንክም፡ በብድር፡ በሚያገኘው፡ ገንዘብ፡ ላይ፡ ሕዝቡ፡ እንዲያጠራቅም፡ አደፋፍሮ፡ ካፒታሉን፡ ለማሳደግ፡ አልሞከረም። ሕዝቡ፡ በባንክ፡ በኩል፡ ለማጠራቀም፡ እንዲደፍር፡ ገንዘብን፡ በጥቅም፡ ላይ፡ የማዋልና፡ ብድር፡ የመስጠት፡ ዘዴ፡ በጣም፡ መሻሻል፡ አለበት። የንጉሠ፡ ነገሥቱም፡ መንግሥት፡ ይህንኑ፡ ሐሳብ፡ መደገፍ፡ ይኖርበታል።

ከዚህ፡ ቀደም፡ ስለ፡ ውጭ፡ ሀገር፡ ገንዘብ፡ ምንዛሬ፡ ቍጥጥር፡ የወጡት፡ ሕጎች፡ የተረጋገጡ፡ ስላልሆኑ፡ የውጭ፡ ሀገር፡ ባለሀብቶች፡ ገንዘባቸውን፡ ኢትዮጵያ፡ ውስጥ፡ በልማት፡ ሥራ፡ ላይ፡ እንዳያውሉ፡ አድርጎአቸዋል። ይሁን፡ እንጂ፡ በዚህ፡ ረገድ፡ የውጭና፡ የሀገር፡ ውስጥ፡ ገንዘብ፡ በልማት፡ ሥራ፡ ላይ፡ እንዲውል፡ ለማበረታታት፡ የወጣው፡ የ፲፱፻፶፯፡ ዓ. ም. ድንጋጌ፡[17] መተማመኛ፡ ሊሆናቸው፡ ይችላል።

በትእዛዝ፡ ቍ፡ ፳፱/፲፱፻፶፰፡ ዓ. ም.[18] የቴክኒክ፡ ድርጅት፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ (ምዕራፍ፡ ፫፡ ቍ. ፱፡ ተመልከት)፡ በእርሻ፡ ሚኒስቴር፡ የአገልግሎት፡ ቅርንጫፍና፡ በቀዳማዊ፡ ኃይለ፡ ሥላሴ፡ ዩኒቨርሲቲ፡ ለቴክኖሎጂ፡ ምርመራና፡ ጥናት፡ እርዳታቸውን፡ ያበረክታሉ። እንደዚሁም፡ በቅርብ፡ ጊዜ፡ በሕዝባዊ፡ ኑሮ፡ እድገት፡ ሚኒስቴር፡ የሥራ፡ ክፍል፡ ሥር፡ የሚያስፈልገውን፡ የሰው፡ ኃይል፡ የሚያጠና፡ የሚያሠለጥንና፡ ለልማትም፡ ዕቅድ፡ እንደሚስማማ፡ አድርጎ፡ የሚያካሂድ፡ "የሰው፡ ኃይል፡ ክፍል"፡ ተቋቁሞአል። ለወደፊቱ፡ በየትኛው፡ ክፍል፡ ምን፡ ያህል፡ ኮሌጅ፡ የጨረሱ፡ ሠራተኞች፡ እንደሚያስፈልጉ፡ ለመገመትና፡

---

17. እላይ፡ የተጠቀሰውን፡ ተመልከት።

18. የቴክኒክ፡ ድርጅት፡ ጽሕፈት፡ ቤት፡ ስለ፡ መቋቋም፡ የወጣ፡ ትእዛዝ፤ ቍጥር፡ ፳፱/፶፰፡ ዓ፡ ም፤ (ነጋሪት፡ ጋዜጣ፡ ፳፪ኛ፡ ዓመት፡ ቍጥር፡ ፲፩)።

የትምህርቱንም ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ ለማኪያሄድ ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥናት ፡ አድርጎ ፡ ነበር ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### የልማት ፡ መመሪያ ፡ (ፖሊሲ) ፡ ለማውጣት ፡ የሚችሉ ፡ ባለሥልጣኖች ፡—

(፩) ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡—

የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ከልማት ፡ መመሪያ ፡ (ፖሊሲ) ፡ አውጪ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሁሉ ፡ የመጨረሻውን ፡ ከፍተኛ ፡ ቦታ ፡ መያዝ ፡ ይገባቸዋል ። በ፲፱፻፵፰ ፡ ዓ. ም. [19] ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሰፊ ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ ይሰጠዋል ።

አንቀጽ ፡ ፷፮ ፡ "ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ የሚሠራባቸውን ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶችንና ፡ የሚኒስቴሮችን ፡ ሁሉ ፡ የሥራ ፡ አኳኋን ፡ አቋቁም ፡ ይወስናል ፤ ....."

ስለዚህ ፡ በኢኮኖሚና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ዕቅድ ፡ በኩል ፡ ለሚያስፈልጉት ፡ ሥራዎች ፡ ሁሉ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሡ ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ ባለሥልጣን፡ በመሾም ፡ ለማስፈጸም ፡ ይችላል ።

> አንቀጽ ፡ ፹፮ ፡- "ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የበላይ ፡ ገዥ ፡ በመሆን፡በማንኛቸውም ፡
> ጊዜ . . . የነዋሪዎቹን ፡ ጥቅምና ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠበቅ ፡
> አስፈላጊውን ፡ ሁሉ ፡ ማድረግ ፡ ተግባሩ ፡ ነው ።....."

የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትና ፡ የልማት ፡ ዕቅዶች ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥና ፡ ውጥኖች ፡ ለነዋሪው ፡ ሕዝብ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆኑ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥራዎች ፡ ናቸው ፤ ሊባል ፡ ይቻላል ።

በሕገ ፡ መንግሥቱ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ መሠረት ፡ ሳይሆን ፡ በያዘው ፡ ወደር ፡ በሌለው ፡ ቦታ ፡ ብቻ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በሌሎች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተሰጡትን ፡ ውሳኔዎች ፡ ሊያሻሽል ፡ ይችላል ። ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ራሳቸው ፡ ከሚያካሂዷቸው ፡ አያሌ ፡ ሥራዎች ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማትና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ከፍተኛውን ፡ ስፍራ ፡ ስለ ፡ ያዙ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤን ፡ በፕሬዚዳንቶች ፡ ይመሩታል ። እንዲሁም ፡ ማንኛውንም ፡ በፓርላማ ፡ የሚወጣውን ፡ ሕግ ፡ ያጸድቃሉ ።

(፪) የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡

"የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጉባኤ ፡ በግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ይመራል ። የጉባኤውም ፡ አባሎች ፡—

> ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ የዘውድ ፡ አማካሪዎች ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩና ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ሚንስት

---

19. በአዋጅ ፡ ቊጥር ፡ ፻፵፱ ፡ የታወጀ ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፲፭ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍ ፡ ፪) ።

ሮች ፡ ናቸው ። ጉባኤው ፡ መመሪያ ፡ (ፖሊሲ) ፡ አውጪ ፡ ሲሆን ፡ ጠቅላላ ፡ የ ኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ሁኔታን ፡ ለመገመትና ፡ አንዳንድ ፡ ትልልቅ ፡ የልማት ፡ ፖሊሲዎችን ፡ ለማውጣት ፡ በየጊዜው ፡ ስብሰባ ፡ ያደርጋል ።[20]

በተሻሻለው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡[21] አንቀጽ ፡ ፸ ፡ መሠረት ፡ በዘውድ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ውስጥ "......ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚመርጣቸው ፡ ልዑላን ፡ መሳፍንት ፡ ሚኒስትሮችና ፡ መኳንንቶች ፡ ይኖሩበታል ።"

ሚኒስትሮች ፡ በሙሉ ፡ ተሰብስበው ፡ የሚገኙበት ፡[22] ጉባኤ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ስለሆነና ፡ ይህም ፡ ጉባኤ ፡ የሚመራው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ እርሳቸው ፡ በሌሉበት ፡ ጊዜ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በመሆኑ ፡[23] ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤም ፡ ውስጥ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ፕሬዚዳንት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ የሚመርጣቸው ፡ ልዑላን ፡ መሣፍንትና ፡ መኳንንት ፡ ይገኛሉ ፡ ማለት ፡ ነው ። አባሎች ፡ ተደማጭነት ፡ አላቸው ፤ ሆኖም ፡ ጉባኤው ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ ለሚሆነው ፡ ሁሉ ፡ ኀላፊነት ፡ የለውም ።

የኢኮኖሚ ፡ ልማትና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ዕቅዶች ፡ እንዴት ፡ መፈጸም ፡ እንደሚገባቸውና ፡ እንዴትስ ፡ እንደሚኪያሄዱ ፡ የሚገልጸውን ፡ ጽሑፍ ፡ የሚያወጣ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የጉባኤው ፡ ውሳኔ ፡ በሞላ ፡ ወይም ፡ በከፊል ፡ በሚጠቅሳቸው ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በግል ፡ ባለንብረቶችና ፡ በጠቅላላው ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነት ፡ ያገኛል ፤ ተብሎ ፡ ይገመታል። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔዎች ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ስለ ሆኑና ፡ አብዛኞቹም ፡ አባሎች ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ስለሆኑ ፡ ይህ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ተበትኖ ፡ ሥራው ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ቢወሰድ ፡ ለአስተዳደር ፡ በጣም ፡ የሚያመች ፡ ይመስላል ። ይኸውም ፡ በሚኒስትሮችና ፡ ሌሎች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ላይ ፡ ከባድ ፡ ሸክም ፡ ስለሚያመጣ ፡ የዚህ ፡ ከፍተኛ ፡ አቋም ፡ አለመኖር ፡ ሥራ ፡ ያቀልላቸው ፡ ይሆናል ። በተጨማሪም ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ አለመኖር ፡ ጊዜ ፡ እንዳይባክን ፡ ያደርጋል ፤ የዕቅድ ፡ ሥራም ፡ ተደጋግሞ ፡ እንዳይሠራ ፡ ያደርጋል ። ይኸውም ፡ አንድ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ ሕግ ፡ ሆኖም ፡ እንዲወጣ ፡ በተፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ መላክ ፡ አይኖርበትም ፤ ማለት ፡ ነው ። በቀጥታ ፡ ከሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወይም ፡ (ሥነ ፡ ሥርዓቱ ፡ እንደሚያዘው) ፡ ወደ ፡ ፓርላማ ፡ ተልኮ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ይቀርባል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ ሲሆን ፡ አንድ ፡ ጠቃሚ ፡ ነገር ፡ በሕግ ፡ እንዲወጣ ፡ ሲፈለግ ፡ በመዠመሪያ ፡ ወደ ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ከመላክ ፡ ያድነዋል ፤ ወደ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤቱ ፡ ጉባኤ ፡ ይሄድና ፡ የሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ወዲያውኑ ፡ ይወጣል ።

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ እንዲተካ ፡ ፕሮፌሰር ፡ አርዘኖዊስኪ ፡ በሰጡት ፡ ሪፖርት ፡ ውስጥ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቦ ፡

---

20. ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ፩ኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፹፮ ።

21. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፲፱ ፡ ተጠቅሷል ።

22. እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ አዋጅ ፡ አንቀጽ ፡ ፳፱ ።

23. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፯ ፡ የተጠቀሰውን ፡ ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ የወጣውን ፡ ትእዛዝ ፡ ለማሻሻል ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ቍ ፡ ፯/፴፭ ፡ (ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ፫ኛ ፡ ዓመት ፡ ቍ ፡ ፩) ።

ነበር ።[24] ነገር ፡ ግን ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ ያለው ፡ ዝንባሌ ፡ ከአስተዳዳሪው ፡ በ ለጥ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ ተገኘ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ሳይለወጡ ፡ በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ሳይለውጡ ፡ ተጨምሮአል ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የዕቅድ ፡ ዋና ፡ ጸሐፊ ፡ ነው ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራዎችና ፡ ሥልጣኖች ፡ ከዚህ ፡ እንደሚከተለው ፡ ተገልጸዋል ፡—

> የዕቅድ ፡ ቦርድ ፡ በዕቅድ ፡ አውጪ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍል ፡ ከተጠናና ፡ የዕ ቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኝ ፡ ጉባኤ ፡ ከተስማማበት ፡ በኋላ ፡ ለማንኛቸውም ፡ የል ማት ፡ ዕቅድ ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ጠቅላላ ፡ በጀት ፡ ያዘጋጃል ። በተጨማ ሪም ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የወጡትን ፡ ዕቅዶች ፡ እንዲቀበ ሉና ፡ እንዲያኪያሂዱ ፡ ለሚጠቅሳቸው ፡ ሁሉ ፡ መምሪያ ፡ እየሰጠ ፡ ዕቅዱም ፡ ያስገኛቸውን ፡ ጥቅሞች ፡ በጽሑፍ ፡ እያዘጋጀ ፡ ያወጣል ።

በትእዛዙ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ "ዕቅድ" ፡ ማለት ፡ በሁለት ፡ ዓመት ፡ ወይም ፡ ከዚያ ፡ በሚበልጥ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ የሚከናወኑትን ፡ የልማት ፡ ሥራዎች ፡ የያዘ ፡ ሐሳብ ፡ (ረቂቅ) ፡ ነው ፤ በማለት ፡ ተገልጿል ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፤ ከፍ ፡ ካለው ፡ ደረጃው ፡ ጋር ፡ ተስማሚ ፡ የሚሆኑትን ፡ ሥራዎች ፡ ብቻ ፡ ይሠራል ፡ ማለት ፡ ነው ። ይህም ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድንና ፡ ከሁለት ፡ ዓመት ፡ ባላነሰ ፡ ጊዜ ፡ ሊሠሩ ፡ የታቀዱትን ፡ ጠቅላላ ፡ ዕቅዶች ፡ ብቻ ፡ ይመለከታል ፡ ማለት ፡ ነው ። እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ ዕቅዶች ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ (ሶሾ—ኢኮኖሚ) ፡ መዝገቦች ፡ ይባላሉ ፤ እነዚህም ፡ የወደፊቱን ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ የሚያሳዩ ፡ ናቸው ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ከዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኝ ፡ ጉባኤ ፡ ወደ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ በመዠመሪያ ፡ ይሄዳል ። ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፓርላማና ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይሄድና ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ ይወጣል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የሥራ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ሠንጠረዥና ፡ የልማት ፡ በጀት ፡ ተቀነባብረው ፡ ሁለቱም ፡ ወደ ፡ አንድ ፡ ግብ ፡ ያመራሉ ።

## (፫) <u>በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፤ (የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኝ ፡ ጉባኤ)</u>

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በየጊዜው ፡ ሪፖርት ፡ ይሰጣል ። በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በዐዋጅ ፡ አልወጣም ። የዚህ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ "የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገትንና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማትንና ፡ ፖሊሲዎች ፡ መስጠት ፤ ለሚኒስትሮች ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለቴክኒካዊ ፡ ድርጅቶች ፡ ወኪሎችና ፡ ለሌሎች ፡ የመንግሥትም ፡ ሆነ ፡ የግል ፡ ባለንብረት ፡ ወኪሎች ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚና ፡ ስለ ፡ ልማት ፡ ጥናቶች ፡ የማያኪያሄድና ፡ ስለ ፡ ዓመታዊ ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዕቅዶች ፡ ሐሳብ ፡ መስጠትን ፡ ይጠቀልላል ። የልማት ፡ ዕቅዶች ፡ በሚገባ ፡ መኪያሄዳቸውንና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ዕቅዶች ፡ ማስተባበራቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ።"[25] የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ እንዳለ ፡

---

24. ቢ ፡ አርዝኖውስኪ ፡— ዘ ፡ ኢንስቲቲውሽናል ፡ ሴትአፕ ፡ ኦፍ ፡ ፕላኒንግ ፡ ኢኮኖሚክ ፡ ዲቨሎፕሜንት ፡ ኢን ፡ ኢትዮጵያ ፤ (ጥቅምት ፡ ፲፱፻፷፫ ፡ እ ፡ ኤ ፡ አ ፡ ያልታተመ) ።
25. ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ፩ኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ገጽ ፡ ፲፱፻፷፩ ።

ይቆይ ፡ ቢባልም ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚውን ፡ ክፍል ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ኮሚቴ ፡ ማድረግ ፡ በጣም ፡ ጥሩ ፡ እርምጃ ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ። ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ የሆኑ ፡ ውሳኔዎችን ፡ መስጠት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ መንግሥት ፡ ፖሊሲ ፡ መተርጐምና ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ድርጅቶችን ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ማስተባበር ፡ ይኖርበታል ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ተመልክቶ ፡ ከአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ ውስጥ ፡ ይገኛሉ ፡ ብሎ ፡ ቢቀበላቸውም ፡ ባይቀበላቸውም ፡ በሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ የሚቀርቡበት ፡ ብዙዎቹ ፡ ሐሳቦች ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ተጠንተው ፡ በሕግ ፡ ረቂቅ ፡ ፎርም ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ። ሥራ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ የሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ክፍል ፡ ቢሆን ፡ ጉባኤው ፡ እንዲያጸድቃቸው ፡ ሪፖርቶቹንና ፡ ሐሳቦቹን ፡ ሲያቀርብ ፡ የሚያቀርባቸው ፡ ሐሳቦች ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ተደጋፊነት ፡ ያገኛሉ ።

በትእዛዙ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኝ ፡ ጉባኤ ፡ መሪ ፡ ሐሳቦችን ፡ የሚያደረጅና ፡ የሚያዳብር ፡ አካል ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ ተገምቶአል ። ይህንም ፡ ሲያደርግ ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዕቅድን ፡ ለማጽደቅ ፡ ኀላፊ ፡ በሆነው ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ኀላፊነት ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ነው ። ለዕቅድና ፡ የሠንጠረዥ ፡ ዝግጅትና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ ለሥራዎች ፡ መስተባበርና ፡ በየትኛውም ፡ ቦታ ፡ ቢሆን ፡ ለሥራው ፡ መፈጸም ፡ የመጨረሻ ፡ ኀላፊ ፡ እሱው ፡ ነው ። በረዥም ፡ ጊዜ ፡ የዕቅድ ፡ መነሻ ፡ መደብ ፡ ውስጥ ፡ ያሉ ፡ የዓመት ፡ ሠንጠረዦች ፡ በዕቅድ ፡ ሥር ፡ አጥኝ ፡ ጉባኤ ፡ ከጸደቁ ፡ በኋላ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አጥንቶአቸው ፡ በመጨረሻ ፡ ፓርላማ ፡ አጽድቋቸው ፡ እንዲደነገጉ ፡ ወደ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይላካሉ ። እነዚህም ፡ ሠንጠረዦች ፡ ከዓመቱ ፡ ባጀት ፡ ጋር ፡ በደንብ ፡ ይተባበሩና ፡ ለዓመቱ ፡ ለሚደረገው ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ ሕጋዊ ፡ መነሻ ፡ መደብ ፡ ይሆናሉ ።

ባሁኑ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ላይ ፡ ያለው ፡ አንዱ ፡ ጉድለት ፡ ሰፊ ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ለማካሄድ ፡ አስቸጋሪ ፡ መሆኑ ፡ ነው ። በጠቅላይና ፡ በጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ሲመራ ፡ የገንዘብ ፡ የእርሻ ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ የሥራና ፡ የመገናኛ ፡ የፖስታ ፡ ቴሌፎንና ፡ ቴሌግራም ፡ የሕዝባዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ የሕዝብ ፡ ጤና ፡ ጥበቃ ፡ የትምህርት ፡ የማስታወቂያ ፡ የማዕድን ፡ ሚኒስትሮችና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክ ፡ ገዥን ፡ በአባልነት ፡ ይጨምራል ።[26] አሁን ፡ በተቋቋመው ፡ አኳኋን ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚው ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ በሆኑት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሊሠራ ፡ ይችላል ። ይህም ፡ አንድ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍልን ፡ ይቀንሳል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ አነስተኛ ፡ ቢሆን ፡ ኖሮ ፡ ጥሩ ፡ የጉዳይ ፡ ማጣሪያ ፡ ክፍል ፡ ይሆን ፡ ነበር ። ይህም ፡ ቢሆን ፡ ይህ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የአገሪቷን ፡ ጥቅም ፡ የሚመለከት ፡ ብሔራዊ ፡ አካል ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ ለተለያዩ ፡ ጥቅሞች ፡ እንደራሴ ፡ የሚወከልበት ፡ አይደለም ፤ ሚኒስትሮች ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በብሔራዊ ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ ውስጥ ፡ ቢኖሩበትም ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜም ፡ ጉዳዩ ፡ ቢመለከታቸው ፡ ሁልጊዜ ፡ በጉባኤው ፡ ላይ ፡ መገኘት ፡ ያስፈልጋቸዋል ፡ ማለት ፡ አይደለም ። የብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ አጥኚው ፡ ጉባኤ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ሲመራ ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ የሚመረጡ ፡ ካራት ፡ የማያንሱ ፡ ከስድስት ፡ የማይበልጡ ፡ ቋሚ ፡ የሚኒስ

26. አላይ ፡ የተጠቀሰው ።

ትር ፡ አባሎች ፡ ይኖሩታል ። በትእዛዙ ፡ ረቂቅ ፡ መሠረት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ባለሥልጣኖችን ፡ የግል ፡ ንግድ ፡ ሥራና ፡ የንግድ ፡ ሥራ ፡ ማኅበሮች ፡ እንደራሴዎችንና ፡ ባንድ ፡ ዐይነት ፡ ሥራ ፡ የተለየ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ በስብሰባው ፡ ላይ ፡ በአማካሪ ፡ ደረጃ ፡ እንዲገኙ ፡ በየጊዜው ፡ ለመጋበዝ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ።

## (፩) <u>የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ።</u>

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ ሚኒስትሮች ፡ ተሰብስበው ፡ የሚገኙበት ፡ ጉባኤ ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ ይባላል ።[27] በጉባኤው ፡ ለሚሰጡት ፡ አስተያየትና ፡ ሐሳብ ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አላፊ ፡ ይሆናሉ ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤና ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ አሁን ፡ ያላቸውን ፡ ሥልጣን ፡ ይዘው ፡ ቢቆዩም ፡ የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ የዕቅድ ፡ መሪ—ሐሳቦችን ፡ በማስፋፋት ፡ ረገድ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ይኖረዋል ። ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦችን ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚወጡትን ፡ ሕጎች ፡ ይመለከታል ። ማንኛቸውንም ፡ ባጀት ፡ ተመልክቶ ፡ መስማማቱን ፡ ይገልጻል ። ለማንኛቸውም ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ለሆነ ፡ ነገር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አማካሪ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የጊዜውን ፡ ሁኔታና ፡ በኢኮኖሚና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ በኩል ፡ የቀረቡትን ፡ ሐሳቦች ፡ በቅርብ ፡ መከታተል ፡ አለበት ። የሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ በሙሉ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎች ፡ ናቸው ። በዚህ ፡ መሠረት ፡ ከአባሎቹ ፡ አብዛኞቹ ፡ እነሱ ፡ መሆናቸው ፡ ነው ። እንደዚሁም ፡ አሁን ፡ ባለው ፡ ሁኔታም ፡ ከሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባሎች ፡ አብዛኞዎቹ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ አባሎች ፡ ናቸው ። ሚኒስትሮችና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ (የሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤያቸው ፡ በሚኒስትሮች ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ የሚመራው) ፡ የልማት ፡ ዕቅድንና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦችን ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ የሚያውሉ ፡ የሥራ ፡ ክፍሎች ፡ ናቸው ።

በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የዓመቱ ፡ የልማት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ከተስማማባቸው ፡ በኋላ ፡ ለፓርላማው ፡ ከመቅረባቸው ፡ በፊት ፡ በሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ መጽደቅ ፡ አለባቸው ፡ ይላል ።

## (፮) <u>ፓ ር ላ ማ ።</u>

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ እንደ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድና ፡ እንደሌሎቹም ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ውጥኖች ፡ ለኅብረ ፡ ሰብ ፡ ኢኮኖሚ ፡ ጽሑፍ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ የሕግ ፡ ጽሑፎች ፡ አይደሉም ። ስለዚህ ፡ ፓርላማ ፡ በነሱ ፡ ጉዳይ ፡ ያለው ፡ ተግባር ፡ ከመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ሆኖ ፡ ውጥኖቹ ፡ የሚካሄዱበትን ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ አጥንቶ ፡ ማጽደቅ ፡ ነው ። ይህ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ በዕቅድ ፡ የሥራ ፡ ዝግጅት ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ቦታ ፡ ቢኖረው ፡ የጠቅላላውን ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ዝግጅት ፡ አይጠቀልልም ። ከሌላ ፡ ምንጭ ፡ በሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ የሚካሄዱትን ፡ ውጥኖች ፡ ካለማስገባቱም ፡ ሌላ ፡ የዓመቱን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ በረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዕቅድ ፡ ውስጥ ፡ አቀናብሮ ፡ አያሳይም ።

በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ከዓመቱ ፡ ባጀት ፡ ጋር ፡ ባንድነት ፡ በፓርላማ ፡ መደንገግ ፡

27. ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፷፬ ።

ይገባዋል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቦአል ። ይህ ፡ ፓርላማውን ፡ ከዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ እንዲኖረው ፡ ከማድረጉም ፡ በላይ ፡ መሪ ፡ ሐሳብ ፡ በመመሥረት ፡ ላይም ፡ በጥልቅ ፡ ገብቶ ፡ እንደሚሠራ ፡ ያረጋግጣል ። ሆኖም ፡ ስለ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድና ፡ ስለ ፡ ረዥምም ፡ ጊዜ ፡ ውጥኖች ፡ ሐሳብ ፡ በየጊዜው ፡ ለፓርላማ ፡ ማስታወስ ፡ አስፈላጊ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ መግለጫዎች ፡ መረጃዎችና ፡ እስታቲስቲኮች ፡ ከፓርላማው ፡ እንዲቀርቡና ፡ ለአባሎቹ ፡ በሰፊውና ፡ በጥንቃቄ ፡ እንዲብራሩ ፡ ያስፈልጋል ።

## ምዕራፍ ፡ ፮ ።

## የዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ክፍሎች ።

### (፩) የዕቅድን ፡ ክፍሎች ፡ መቈጣጠርና ፡ ማስተባበር ።

የዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የአስተዳደር ፡ ክፍሎችና ፡ ዕቅድን ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ ጊዜ ፡ የሚረዱት ፡ የቴክኒክ ፡ ክፍሎች ፡ ለልማት ፡ እድገት ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ስለሆኑ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ እነዚህን ፡ ሥራዎች ፡ የሚመራ ፡ አንድ ፡ አዲስ ፡ የልማት ፡ ሚኒስትር ፡ ዴኤታ ፡ መሾም ፡ አለበት ። በዕቅድ ፡ ረገድ ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩን ፡ ማንኛቸውንም ፡ ሥራዎች ፡ ያካሂዳል ፤ ሆኖም ፡ የተወሰደው ፡ እርምጃ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ መጽደቅ ፡ አለበት ። በተጨማሪም ፡ ከሌሎቹ ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሥራ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ የወጡት ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋዋላቸውን ፡ መቈጣጠር ፡ እንዲቻል ፡ ትክክለኛ ፡ መረጃ ፡ ማግኘታቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይረዳል ።

### (፪) በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የቴክኒክ ፡ አስተባባሪ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የቴክኒክ ፡ አስተባባሪ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ "የተቋቋመው ፡ በሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ (በቦርዱ) ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ሹም ፡ ሊቀ ፡ መንበርነት ፡ ነው ። አባሎቹም ፡ በየሚኒስቴሮች ፡ ውስጥ ፡ ለተቋቋሙት ፡ የዕቅድ ፡ ክፍል ፡ ወይም ፡ በኢኮኖሚና ፡ በማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሥራ ፡ የመንግሥት ፡ ወኪሎች ፡ ለሆኑ ፡ ሹሞች ፡ ናቸው ። ይህ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የቀረቡትን ፡ ማንኛቸውንም ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተያየቶች ፡ አጥንቶና ፡ መርምሮ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍሎች ፡ አስተያየቱን ፡ ያቀርባል ።" [28]

ይህ ፡ ተግባር ፡ ከሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ይልቅ ፡ ለአስተዳዳሪዎች ፡ የሚስማማ ፡ ይመስላል ። በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ ሥራ ፡ የነበረው ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተሰጥቶአል ።

### (፫) የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።

"የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ (ማለት ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት) ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪና ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ ዋና ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ነው ። የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎችን ፡ በጠቅላላ ፡ የሚያገ

28. ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ፩ኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፰፭ ።

ለግሉ ፡ የቴክኒክ ፡ ሠራተኞች ፡ አሉት ። ይህ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከጠቅላይ ፡ የስታትስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከቴክኒክ ፡ ድርጅት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከእያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዩኒቨርሲቲ ፡ ከልማት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤትና ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ ከሚያዘጋጁ ፡ ከሌሎች ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ ሥራውን ፡ ያካሄዳል ። በተጨማሪም ፡ የወጡት ፡ ዕቅዶች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ እንደሚውሉ ፡ የቀረበውን ፡ ጥናት ፡ በጥቅም ፡ ላይ ፡ የዋሉትን ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ምርመራ ፡ ጥናት ፡ ጽሑፎችንና ፡ የሚካሄዱትን ፡ የማሠልጠኛ ፡ ኮርሶች ፡ ይመለከታል ።” [29]

ይህ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ሊደረብ ፡ ወይም ፡ ራሱን ፡ የቻለ ፡ አንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሆኖ ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ። እያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጥሩ ፡ አስተዳደር ፡ እንዲኖረው ፡ ሕግ ፡ መከበሩንና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላላና ፡ ፖለቲካዊ ፡ ጉዳይ ፡ በደንብ ፡ ማካሄዱን ፡ ማረጋገጥ ፡ የጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ኀላፊነት ፡ ስለሆነ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትም ፡ በሱው ፡ ሥር ፡ ይሁን ፡ ቢባል ፡ ትክክለኛ ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ራሱን ፡ የቻለ ፡ ሌላ ፡ ሚኒስቴር ፡ ማቋቋም ፡ የሥልጣን ፡ ጭቅጭቅን ፡ ይፈጥር ፡ ይሆናል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ባሉት ፡ ሥልጣኖችና ፡ ኀላፊነት ፡ መሠረት ፡ ሥራዎቹ ፡ የተወሰኑ ፡ ሲሆኑ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራዎች ፡ ደግሞ ፡ ሰፊና ፡ ወሰን ፡ የሌላቸው ፡ ስለሆኑ ፡ ሁለቱን ፡ ተቃራኒ ፡ ተግባር ፡ ያላቸውን ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ባንድነት ፡ ማድረግ ፡ አስቸጋሪ ፡ ይሆናል ።

የብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ቦታና ፡ ደረጃ ፡ የት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይገልጽም ። የት ፡ እንደሚገኝ ፡ ጥቂት ፡ ፍንጭ ፡ የሚሰጠው ፡ «የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባጀት ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ባጀት ፡ ሥር ፡ ራሱን ፡ በቻለ ፡ አርእስት ፡ ይሆናል ፤ የጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ የውስጥ ፡ አቋም ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ቀርቦ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ይጸድቃል ፤» የሚለው ፡ ደንብ ፡ ነው ። ደግሞም ፡ «የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ማዕርግ ፡ በምክትል ፡ ሚኒስቴር ፡ ደረጃ ፡ ወይም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ይሆናል ። የሚሾመውም ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ነው ፤» ይላል ። በማን ፡ እንደሚታዘዝ ፡ የሚያሳይ ፡ ምንም ፡ ነገር ፡ የለም ።

የትእዛዙ ፡ ረቂቅ ፡ ታርሞ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ለማንኛውም ፡ ተግባሩ ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ፤ እንዲል ፡ ያስፈልጋል ። ሆኖም ፡ የጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ አቋም ፡ አስተዳደር ፡ በባጀት ፡ ዝግጅትና ፡ ባጀትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በማዋል ፡ በኩል ፡ ለጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ ሹም ፡ ሰፋ ፡ ያለና ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሰጠው ፡ ያስፈልጋል ።

በብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ እንደተዘረዘረው ፡ ጠቅላላ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራዎች ፡ የሚቀጥሉት ፡ ናቸው ።

(፩) በጠቅላላ ፡ በተሰጠው ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ግዴታዎችንና ፡ ሥራዎችን ፡ መፈጸም ።

(፪) የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ፖሊሲ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የተወሰነውን ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ በዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡

29. ኣላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ ዕቅድ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፳፪ ።

የዕቅድ ፡ ማስፋፊያ ፡ መምሪያ ፡ አዘጋጅቶ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ጸድቆ ፡ እንዲወጣ ፡ ያደርጋል ።

(፫) ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤና ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጸድቅ ፡ የሚፈለገውን ፡ የተስተባበረውን ፡ የያንዳንዱን ፡ ልማት ፡ ዕቅድ ፡ ያዘጋጃል ።

(፬) ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ የሚጸድቅ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተወሰነው ፡ የልማትና ፡ እድገት ፡ ዕቅድ ፡ መሠረት ፡ በየዓመቱ ፡ እንዲ ፈጸሙ ፡ የታቀዱትን ፡ ዐላማዎች ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ያዘጋጃል ።

(፭) የልማት ፡ ኀብሮችን ፡ በክፍሎችና ፡ በቀጠናዎች ፡ ደረጃ ፡ የሥራ ፡ ሠን ጠረዥ ፡ በማውጣትና ፡ በማስተባበር ፡ መርዳት ።

(፮) ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ እንዲጠቃለሉና ፡ እንዲስተባበሩ ፡ መርዳትና ፡ ማድረግ ፡ በተጨማሪም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የተዘጋጁትን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ በሰፊው ፡ በቀጠና ፡ ደረጃ ፡ በቀ ጠናው ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድ ገት ፡ የሚያጠቃልል ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ማውጣት ።

(፯) በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ለጊዜው ፡ የሚጸድቅ ፡ የተጠቃለለ ፡ የዓመት ፡ የልማት ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ለማውጣት ፡ እንዲረዳ ፡ በቀ ጠና ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የሚዘጋጀውን ፡ የያንዳንዱን ፡ የአውራጃ ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በማስተባበር ፡ መርዳት ።

(፰) የያንዳንዱን ፡ መሥሪያ ፡ የልማት ፡ ባጀት ፡ ግምት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በርዳታ ፡ መልክ ፡ የሚገኘውን ፡ ከሌላም ፡ ያገር ፡ ውስጥ ፡ ገቢ ፡ ምን ጮች ፡ ለልማት ፡ ዕቅድ ፡ የሚውለውን ፡ ባጀት ፡ አስተባብሮ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ማድረግ ።

(፱) ከያንዳንዱ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የሚመጡትን ፡ መግለጫ ዎችና ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የዓመቱ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ በግብር ፡ ላይ ፡ ስለሚውልበት ፡ ዘዴ ፡ የሰጡአቸውን ፡ አስተያየቶች ፡ ተመልክቶ ፡ መከታተልና ፡ በነዚሁም ፡ መግለጫዎች ፡ አስተያየቶች ፡ መሠረት ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ ለውጥ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ።

(፲) የዓመቱን ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋሉን ፡ የሚያሳይ ፡ መግ ለጫ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማቅረብ ። ይህም ፡ መግለጫ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩትን ፡ እንዲይዝ ፡ ያስፈልጋል ።

(ሀ) በተለይ ፡ የዓመቱ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ከዕቅዱ ፡ ጋር ፡ ያለው ፡ ግንኙነት ፡ በአገርና ፡ በክፍለ ፡ አገር ፡ በቀጠና ፡ ከፍተኛ ፡ ወይም ፡ አነስተኛ ፡ ቦታ ፡ ተሰጣቸው ፡ የሚባሉትን ፡ ዕቅዶች ፡ ዝርዝር ፡ የሚይዝ ፡ የዓመቱን ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ በግ ብር ፡ ላይ ፡ አዋዋል ፡ የሚያሳይ ፡ ዝርዝር ፡ ጥናትና ፡ አስተያየት ።

(ለ) ለአገሩ ፡ በጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ለክፍለ ፡ አገሩ ፡ ወይም ፡ ለቀጠናው ፡ ኢኮኖሚ ፡ ይህ ፡ በዓመቱ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ያለውን ፡ ይሰጣል ፡ ተብሎ ፡ የተገመተው ፡ ጥቅም ፡ የመጨረሻው ፡

መግለጫ ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ ጥቅም ፡ ላይ ፡ የተደረገውን ፡ ለውጥና ፡

(ሐ) የያንዳንዱን ፡ የልማት ፡ ኅብረት ፡ ሥራ ፡ ዝርዝር ፡ አስተያየት ።

(፲፩) ዕቅዶች ፡ እንዴት ፡ ከአገሩ ፡ ሁኔታ ፡ ጋር ፡ እንደተዘጋጁና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንደዋሉ ፡ የሚያሳይ ፡ የዓመቱን ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ የሚገልጽ ፡ ባገሩ ፡ ውስጥና ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ለሕዝቡ ፡ የሚሰራጭ ፡ በየጊዜው ፡ የሚወጣ ፡ መጽሔት ፡ ማዘጋጀት ።

ተግባሮቹንና ፡ ሥራዎቹን ፡ በሙላ ፡ እንዲያከናውን ፡ ከተሰጠው ፡ ጠቅላላ ፡ ሥልጣን ፡ ሌላ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚቀጥሉት ፡ ሥልጣኖች ፡ ተሰጥተውታል ።

(ሀ) የልማት ፡ ኅብሮች ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ በሚያወጡበት ፡ ሥራቸውንና ፡ ተግባራቸውን ፡ በሚፈጽሙበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከታተሉዋቸውን ፡ ደንቦች ፡ ማውጣት ።

(ለ) በሥራው ፡ የሠለጠኑ ፡ የቴክኒክ ፡ ዕውቀት ፡ ያላቸውንና ፡ እንዲሁም ፡ ሌሎች ፡ የተማሩ ፡ አማካሪዎችን ፡ በልማት ፡ ዕቅድ ፡ ውስጥ ፡ በጠቅላላ ፡ ወይም ፡ ለተለዩ ፡ ነገሮች ፡ ምክር ፡ እንዲሰጡና ፡ ርዳታ ፡ እንዲያበረክቱ ፡ መሾም ።

(ሐ) የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹሞችና ፡ የቀጠናው ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ አዘጋጅተው ፡ በሚያቀርቡበት ፡ ጊዜ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የጸደቀውን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ መከታተላቸውን ፡ ማረጋገጥ ።

(መ) የቀጠና ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሹሞች ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ጠቀስ ፡ የሆነውን ፡ ማንኛቸውንም ፡ አስፈላጊ ፡ ዝርዝርና ፡ መግለጫ ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ማድረግ ።

(ሠ) በጠቅላላ ፡ እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በ"ትእዛዝ" ፡ ወይም ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በተሰጠው ፡ መምሪያ ፡ መሠረት ፡ ማንኛቸውንም ፡ ግዳጃቸውን ፡ መፈጸማቸውን ፡ ማረጋገጥ ።

ምንም ፡ እንኳ ፡ የዕቅዱ ፡ ክፍሎች ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ ሥራቸውን ፡ በሚያካሂዱበት ፡ ጊዜ ፡ ከዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ እንዲተባበሩ ፡ ግዳጃቸው ፡ ቢሆንም ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መረጃዎችን ፡ እንዲያቀርቡ ፡ ለማስገደድ ፡ የሚያስችል ፡ ሥልጣን ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። አብዛኛዎቹ ፡ የክፍል ፡ አለቆች ፡ ከዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የበለጠ ፡ ከፍተኛ ፡ ሥልጣን ፡ ስላላቸው ፡ ይህ ፡ የማስገደድ ፡ ሥልጣን ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስቴሩ ፡ ተሰጥቶ ፡ በሳቸው ፡ ስም ፡ ቢሠራበት ፡ ይሻላል ። በጣም ፡ ሊታሰብበት ፡ ወይም ፡ ሊታወቅ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ዕቅድ ፡ ማውጣት ፡ በደንብ ፡ የሚከናወነው ፡ የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ ሥልጣን ፡ ሳይጠቀሙ ፡ የሚፈልጉትን ፡ መረጃና ፡ መተባበር ፡ የሚያስገኝ ፡ እርስ ፡ በርስና ፡ በሥራ ፡ በኩልም ፡ ጥሩ ፡ የመግባባት ፡ ፈሊጥ ፡ የተመሠረተ ፡ እንደሆን ፡ ነው ።

ለወደፊት ፡ አስፈላጊውን ፡ ለውጥ ፡ ለማድረግ ፡ እንዲቀል ፡ ስለ ፡ ዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አቋም ፡ ያሉት ፡ ጥቃቅንና ፡ ዝርዝር ፡ ነገሮች ፡ እንዲሁም ፡ የን

ዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ሥራ ፡ በሕጉ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ተገድፈዋል ፤ ሆኖም ፡ እነዚህን ፡ ዝርዝርና ፡ ጥቃቅን ፡ ነገሮች ፡ በውስጥ ፡ ደንብ ፡ መገለጽ ፡ አለባቸው ።

በኔ ፡ አስተያየት ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሦስት ፡ ክፍሎች ፡ እንዲኖሩት ፡ ያሻል ፡— እነኝሁም ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ምርመራና ፡ ጥናት ፡ ክፍል ፡ የማስተባበሪያና ፡ የጉዳይ ፡ መከታተያ፡ ክፍልና ፡ የአስተዳደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ክፍል ፡ ናቸው ።[30]

<u>የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ምርመራና ፡ ጥናት ፡ ክፍል</u> ፡ በአራት ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ሊቋቋም ፡ ይችላል ።

(፩) <u>የምርመራና ፡ የጥናት ፡ ንዑስ ፡ ክፍል</u> ፡ ኢኮኖሚ ፡ ጥናት ፡ እያደረገ ፡ የተገኘውን ፡ ውጤት ፡ ለሌሎች ፡ የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ ያበረክታል ። ለያንዳንዱ ፡ መካከለኛና ፡ የረዥም ፡ ጊዜ ፡ ዕቅድ ፡ (ንዑስ ፡ ክፍሉ) ፡ መረጃዎችን ፡ ከሌሎቹ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ኅብሮችና ፡ ከውጭ ፡ የዕቅድ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መሰብሰብና ፡ እንዲሠራበት ፡ የታቀደውን ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ፖሊሲን ፡ መወሰን ፡ በፓርላማ ፡ የተደነገጉትን ፡ ሕጎች ፡ በግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ የተሰጡትን ፡ መሪ ፡ ቃሎችና ፡ በከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የተደረጉትን ፡ ንግግሮች ፡ ማጥናት ፡ አለበት ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እነዚህን ፡ ፖሊሲዎች ፡ መሠረት ፡ በማድረግ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ዕቅዶቹን ፡ የሚያብራሩበትን ፡ መምሪያ ፡ ማርቀቅ ፡ ይችላል ። እነዚህም ፡ መምሪያዎች ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርበው ፡ ከጸደቁ ፡ በኋላ ፡ በተገቢው ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ይተላለፋሉ ፤ ንዑስ ፡ ክፍሉም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በተወሰነው ፡ ዕቅድ ፡ መሠረት ፡ የየዓመቱን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ዓላማ ፡ ያዘጋጃል ።

(፪) <u>የስታቲስቲክ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል</u> ፡ በጥናትና ፡ ምርመራ ፡ ንዑስ ፡ ክፍልና ፡ በማስታወቂያ ፡ ክፍል ፡ የሚፈለጉትን ፡ እስታቲስቲኮች ፡ አዘጋጅቶ ፡ በሠንጠረዥ ፡ ያቀርባል ፤ እንዲሁም ፡ ለኢኮኖሚ ፡ ተጨማሪ ፡ ማዳበሪያንና ፡ ለዕቅዶች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ስሌት ፡ ይሠራል ። ይህም ፡ ምርመራና ፡ ጥናት ፡ ከማስፈለጉ ፡ በላይ ፡ በየመሥሪያ ፡ ቤቱ ፡ እየሄዱ ፡ ዝርዝሮችን ፡ መሰብሰብ ፡ ይጠይቃል ። የዚህ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ሥራ ፡ የጠቅላይ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትን ፡ ሥራ ፡ በድጋሚ ፡ ለመሥራት ፡ ሳይሆን ፡ የሚያገለግለው ፡ ከላይ ፡ ከተጠቀሰው ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚገኘውን ፡ እስታቲስቲክስ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሚፈልገው ፡ መሠረት ፡ ለማስተካከልና ፡ ለማሟላት ፡ ነው ።

(፫) <u>የማስታወቂያ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል</u> ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚደረገው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አስፈላጊ ፡ መሆኑን ፡ በመግለጽና ፡ ከፍተኛ ፡ የፍላጎት ፡ ስሜትን ፡ በመፍጠር ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሥራን ፡ ያከናውናል ።

የማንበብ ፡ ፍላጎት ፡ የሚያሳድሩ ፡ ለሕዝብ ፡ የሚታደሉ ፡ ዓመታዊ ፡ መግለጫዎችን ፡ ለዜና ፡ ማሰራጫዎች ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ በሚገባው ፡ አነጋገር ፡ አዘጋጅቶ ፡ ማቅረብና ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቶችና ፡ በያውራጃው ፡ በሚገኙት ፡ የመንግሥት ፡ ወኪሎች ፡ እንዲነገሩ ፡ ማድረግ ፡ ይኖርበታል ። <u>የማሠልጠኛ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል</u> ፡ ለልማት ፡ ኅብረት ፡ ሠራተኞችና ፡ ለሌሎች ፡ የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ የተለየ ፡ የትምህርት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ ልምምድ ፡ ያደራጃል ። <u>የማስተባበሪያና ፡ ተከ</u>

30. እታች ፡ ፫ኛ ፡ ተጨማሪውን ፡ ተመልከት ።

ታትሎ ፡ የማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ በስድስት ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ የክፍለ ፡
አገር ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ ሊከፈል ፡ ይችላል ። የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ በሥራ
ቸው ፡ ዓላማ ፡ ከቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ጋር ፡ መመሳሰል ፡ አለ
ባቸው ። እነዚህም ፡ የኢንዱስትሪ ፡ የኀይልና ፡ የማዕድን ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የእርሻ ፡
ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የሕንጻና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎች ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የማመላለሻና ፡
የመገናኛ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ የንግድና ፡ የሕዝብ ፡ አገልግሎት ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡
ናቸው ።

(፭) እነዚህ ፡ ስድስቱ ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍሎች ፡ እያንዳንዳቸው ፡ በየቀ
ጠናቸው ፡ በአምስቱ ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ መሠረት ፡ የመዠመሪያውን ፡
ርምጃ ፡ መውሰድ ፡ አለባቸው ። በራሱ ፡ ቀጠና ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡
የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የእድገት ፡ ኀብሮቻቸው ፡ ዕቅዶቹን ፡
የሚያስፋፉባቸውን ፡ መምሪያዎች ፡ ይልካል ። ይህም ፡ መምሪያ ፡ እያ
ንዳንዱ ፡ ክፍል ፡ ሐሳቡን ፡ በሚያቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የሚከተላቸውን ፡
ጠቅላላ ፡ ፖሊሲዎች ፡ ይገልጻል ። ክፍሎቹ ፡ ሐሳባቸውን ፡ ለቀጠናቸው ፡

የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ካቀረቡ ፡ በኋላ ፡ ሥራ ፡ አጥኚው ፡
ጉባኤ ፡ የራሱን ፡ ሐሳብ ፡ ያቀርባል ። የሁለቱም ፤ የክፍሎችና ፡ የቀጠና ፡
የእድገት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሐሳቦች ፡ በተገቢው ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡
ክፍል ፡ ከተጠኑ ፡ በኋላ ፡ ከአስተያየታቸው ፡ ጋር ፡ እንደገና ፡ ተጠንተው፡
ተጠቃለው ፡ አንድ ፡ ሆነው ፡ ወደሚወጡበት ፡ ወደ ፡ ክፍሎች ፡ ጠቅላይ ፡
መምሪያ ፡ ይላካሉ ።

እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ በዚያው ፡ ቀጠና ፡ የሚገኘውን ፡ የቀ
ጠና ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤና ፡ በሥራ ፡ አጥኚው ፡ ጉባኤ ፡ አካባቢ ፡ ለሚ
ገኙት ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የዓመቱን ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ በሚያ
ብራሩበት ፡ ጊዜ ፡ እርዳታ ፡ ይሰጣል ። የመጨረሻው ፡ የቀጠናው ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡
በሥራ ፡ አጥኚው ፡ ጉባኤው ፡ ከቀረበ ፡ በኋላ ፡ ንዑስ ፡ ክፍሉ ፡ ከክፍለ ፡ አገሩ ፡
ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ከተቀበለው ፡ አስተያየት ፡ ጋር ፡ ያመዛዝነዋል ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡
የተጠቃለለው ፡ የቀጠናው ፡ የዓመት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ለክፍሎች ፡ ጠቅላይ ፡
መምሪያ ፡ እንዲያስተባብር ፡ ይላካል ።

እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ በቀጠናው ፡ ውስጥ ፡ በመንግሥት ፡
መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ሥር ፡ የሚገኙትን ፡ ክፍሎች ፡ የሥራውን ፡ አፈጻጸም ፡ መከታ
ተል ፡ እንዲችሉ ፡ በየሦስት ፡ ወሩና ፡ በዓመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሚወጡ ፡ መግለ
ጫዎችን ፡ በማሰናዳት ፡ ይረዳቸዋል ። እነዚህን ፡ መግለጫዎች ፡ የዓመቱን ፡ የዕ
ቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ውጤት ፡ ለማጠቃለል ፡ ወደ ፡ ክፍሎች ፡ ጠቅላይ ፡
መምሪያ ፡ ይልካል ።

(፮) የክፍለ ፡ አገሩ ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ሹሞች ፡ ሐሳብ ፡ መሠ
ረት ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሠራተኞችን ፡ ያቀርባል ፤ ከያንዳንዱ ፡
ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ በየቀጠናው ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ስለሚያስፈልጉት ፡
ነገሮች ፡ መረጃን ፡ በመሰብሰብ ፡ ከኢኮኖሚ ፡ ይልቅ ፡ ጂኦግራፊን ፡
ጠቀስ ፡ የሆኑ ፡ በቀጠናው ፡ ከቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ሌላ ፡ አዲስ ፡ ነገሮችን ፡
የሚጨምር ፡ አስተያየት ፡ ንዑስ ፡ ክፍሉ ፡ ሊያቀርብ ፡ ይችላል ።

በጠቅላላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ በሚገኙት ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ቀጠናዎች ፡ በተ
ለይ ፡ ደግሞ ፡ በሥሩ ፡ ለሚገኘው ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ኢኮኖሚ ፡

እድገት ፡ ለየጠቅላይ ፡ ግዥው ፡ በሰፊው ፡ በየጊዜው ፡ መግለጽ ፡ የክፍሉ ፡ አገር ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ተግባር ፡ ነው ። ንዑስ ፡ ክፍሉ ፡ የጠቅላይ ፡ ግዥው ፡ ሐሳቦች ፡ በቀጠናው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ከቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ጋር ፡ ለማስተባበር ፡ እንዲቻል ፡ ወደ ፡ ቀጠናው ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ይላካል ።

የማስተባበሪያና ፡ ተከታትሎ ፡ የማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ ሹም ፡ ከመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በቀጥታ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ለጊዜው ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በጸደቀው ፡ መሠረት ፡ የመዠመሪያ ፡ የባጀትና ፡ የውጭ ፡ ግምታቸውን ፡ ይቀበላል ፤ ደግሞ ፡ ከገንዘብ ፡ ነክ ፡ ድርጅቶችና ፡ ለኢኮኖሚ ፡ እድገት ፡ የተጠየቀውን ፡ የብድር ፡ ገንዘብ ፡ ልክና ፡ ከገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደግሞ ፡ ለሚመጣው ፡ ዓመት ፡ ለልማት ፡ ሥራ ፡ ያለውን ፡ ገንዘብ ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ ከሚሰጠው ፡ እርዳታ ፡ ጭምር ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይነግረዋል ። እነኝህን ፡ ሁሉ ፡ ግምቶች ፡ ለጊዜው ፡ ከጸደቀው ፡ የዓመት ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ጋር ፡ ያተስባብራል ።

የአስተዳደራዊ ፡ አገልግሎት ፡ ክፍል ፡ ለዕቅድ ፡ አስተዳደር ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ማንኛቸውንም ፡ አስተዳደራዊ ፡ የውስጥ ፡ ዝግጅቶች ፡ ይፈጽማል ።

## (፬) <u>የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ (ኮሚቴዎች) ።</u>

የሁለተኛው ፡ ጊዜ ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ስድስት ፡ ቋሚ ፡ ጉባኤዎች ፡ እንዲኖሩት ፡ ተወስኗል ።

(፩) የዕቅድና ፡ ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ የሚያውል ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

(፪) የብድር ፡ ገንዘብ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

(፫) የንግድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

(፬) የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

(፭) የመሬት ፡ አያያዝና ፡ መሻሻልና ፡ የሕዝብ ፡ ማስፈር ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

(፮) የሕግ ፡ አውጭ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ።

እነኝህ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ በልማት ፡ ዕቅድ ፡ በኩል ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጣቸው ፡ የታሰቡትን ፡ ቀጠናዎች ፡ በሙሉ ፡ አይሸፍኑም ። የገንዘብና ፡ የሕግ ፡ ማውጣት ፡ ጉዳይ ፡ ለምሳሌ ፡ በዕቅድ ፡ ከተሸፈነው ፡ ቀጠና ፡ ጋር ፡ ሲታይ ፡ ሲገባው ፡ እንዱስትሪ ፡ ኃይል ፡ የማዕድን ፡ ምንጮች ፡ እርሻ ፡ ማመላለሻና ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የመሐንዲስ ፡ ሥራዎች ፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ በተቋቋመው ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ መሠረት ፡ ጥሩ ፡ ቦታ ፡ የተሰጣቸው ፡ አይመስልም ። ስለዚህ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተዘረዘሩት ፡ የቀጠና ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥር ፡ ባለው ፡ በማስተባበሪያና ፡ ተከታትሎ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ ውስጥ ፡ እንዲቋቋም ፡ ከታሰበው ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ጋር ፡ በማያያዝ ፡ መቋቋም ፡ አለባቸው ።

(፩) እንዱስትሪ ፡ ኃይልና ፡ ማዕድን ።

(፪) እርሻ ።

(፫) ማመላለሻና ፡ መገናኛ ።

(፬) ሕንጻና ፡ ሌሎች ፡ የመሐንዲስ ፡ ሥራዎች ።

(፭) ንግድ ።

(፮) የሕዝብ ፡ አገልግሎት ።

እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ቀጠናውን ፡ በሙሉ ፡ እንዲሁም ፡ ከቀጠናው ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ያላቸውን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ የዋሉ ፡ ገንዘቦችና ፡ የገንዘብ ፡ ጉዳዮች ፡ ድንጋጌዎች ፡ የመሬት ፡ ጥቅምንና ፡ የሰው ፡ ኃይ ልን ፡ የሚመለከት ፡ አካል ፡ ነው ። በቀጠናው ፡ ውስጥ ፡ የሚገፋትን ፡ የሥራ ፡ ሠን ጠረዦች ፡ ውጥኖች ፡ እያስተባበረ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ ያሉትን ፡ ፍላጎቶች ፡ ያመዛዝናል ፤ የብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ አስተዳደር ፡ ትእዛዝ ፡ ረቂቁ ፡ የዚህን ፡ የቀጠና ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ መቋቋም ፡ ያዛል ። የነዚህ ፡ የያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ጉዳይ ፡ ከሚጠቅሰው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የበላይ ፡ ባለሥልጣን፡ የሆነው ፡ ሲሆን ፡ አባሎች ፡ የቀጠናው ፡ ልማት ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ የልማት ፡ ኅብረት ፡ ሹሞች ፡ ለአንዳንድ ፡ ችግሮች ፡ መፍትሔ ፡ ይሰጣሉ ፡ የተባሉ ፡ ዐዋቂ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ያዲስ ፡ አበባው ፡ የነጋዴዎች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ተጠሪዎችና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዡ ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ ያንዳንድ ፡ የግል ፡ ነጋዴዎች ፡ ወኪሎች ፡ ይሆናሉ ። ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤው ፡ በሊቀ ፡ መንበሩ ፡ በኩል ፡ ለጠቅላይ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መግለጫ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ።

የቀጠና ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ እያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ሐሳብ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ የሚጨበጥና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ መሆኑን ፡ ለተወሰኑ ፡ የመንግሥት ፡ ቤቶች ፡ መመደቡንና ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ መወሰኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ። የአፈጻጸማቸውን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ መወሰን ፡ በተለይ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ የተወሰኑት ፡ ውጥኖች ፡ ሁሉ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ በቂ ፡ ካፒታል ፡ ወይም ፡ ሌላ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጮች ፡ ያልተገኙ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የትኞቹ ፡ ውጥኖች ፡ እንደሚሰረዙ ፡ ወይም ፡ ለሌላ ፡ ጊዜ ፡ እንደሚ ተላለፉ ፡ ወይም ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ የተገኘ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የትኞቹ ፡ ተጨማሪ ፡ ውጥኖች ፡ መሠራት ፡ እንዳለባቸው ፡ ስለሚወስን ፡ ነው ።

በያንዳንዱ ፡ ቀጠና ፡ የሚገኙት ፡ በአምስቱ ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ በመጨረሻ ፡ የጸደቁት ፡ ውጥኖች ፡ ለየዓመቱ ፡ መከፋፈል ፡ አለባቸው ። ይህም ፡ በዕቅዱ ፡ ጊዜ ፡ የያንዳንዱ ፡ ቀጠና ፡ ውጥን ፡ የቱን ፡ ያህል ፡ በዓመቱ ፡ ሥራ ፡ ሠንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ እንደሚገባ ፡ ግልጽ ፡ ይሆናል ። የዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦች ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋልን ፡ ጥሩ ፡ አርጎ ፡ ማመዛዘን ፡ የሚቻለው ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ ነው ። ይህ ፡ እንደዚህ ፡ ዐይነቱ ፡ መከፋፈል ፡ ለመቆጣጠር ፡ ተከታትሎ ፡ ለማስፈ ጸምና ፡ ስለ ፡ ዕቅድና ፡ ስለ ፡ ፕሮግራሙ ፡ ውጤት ፡ አስተያየት ፡ ለመስጠት ፡ ያስ ችላል ።

(፭) የልማት ፡ ኅብሮች ፡ በሚኒስቴሮችና ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወኪ ሎች ፡ ውስጥ ፡ ዕቅዶች ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦችና ፡ ውጥኖች ፡ ሊስፋፉና ፡ በሥራ ፡ ሊውሉ ፡ እንዲችሉ ፡ የመዠመሪያው ፡ ኀላፊነት ፡ የሚወድቀው ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ላይ ፡ ነው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የልማት ፡ ዕቅድ ፡ ጥሩ ፡ ውጤት ፡ የሚሰጠው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ጥሩ ፡ ሆኖ ፡ በተቋቋመ ፡ የአስተዳደር ፡ ድርጅትና ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ፈሊጥ ፡ ላይ ፡ ቢጣል ፡ ደንበኛ ፡ የሆኑ ፡ የልማት ፡ ኅብሮችን ፡ ማቋቋምና ፡ በነሱ ፡ መጠቃለልም ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ።

የአምስቱን ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ [31] የሚያስተዋውቀው ፡ ጽሑፍ ፡ ስለ ፡ ልማት ፡ ኀብሮች ፡ ሥራ ፡ በሚናገርበት ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ የሚከተለውን ፡ ይዘረዝራል ።

"የልማት ፡ ኀብሮች ፡ የተቋቋሙት ፡ በሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ሚኒስቴሮችና ፡ ወይም ፡ በመንግሥቱ ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣን ፡ በሚመሩት ፡ ወኪሎች ፡ ውስጥ ፡ ነው ፤ የዕቅድ ፡ ኀብሮች ፡ ተግባር ፡ የሚኒስቴሮቻቸውንና ፡ የወኪሎቻቸውን ፡ ሥራዎች ፡ ማቀድ ፡ የልማቱን ፡ ዕቅድ ፡ አፈጻጸምና ፡ ክፍሎችን ፡ ማስተባበር ፡ መከታተል ፡ ነው ። እነዚህ ፡ የዕቅድ ፡ ኀብሮች ፡ ከዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ ቀጥታ ፡ ግንኙነት ፡ አላቸው ። የያንዳንዱ ፡ የዕቅድ ፡ ኀብረት ሹም ፡ ከበላይ ፡ በሚገኘው ፡ ሚኒስቴር ፡ ትእዛዝ ፡ ሥር ፡ ነው ። እንዲሁም ፡ የልማት ዕቅድ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ እነኝህም ፡ ዕቅዶች ፡ በሚተባበሩበትና ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ በሚውሉበት ፡ ጊዜ ፡ የምርመራ ፡ ጥናትና ፡ የማሠልጠኛ ፡ ኮርስ ፡ በሚሰጥ በት ፡ ጊዜ ፡ ከነዚህ ፡ ጋር ፡ ግንኙነት ፡ ለማድረግ ፡ ኀላፊ ፡ ነው ። ..."

በጥቂቶቹ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ እነኝህ ፡ የዕቅድ ፡ ኀብ ሮች ፡ በደንብ ፡ ሥራቸውን ፡ ያካሂዳሉ ። በሌሎቹ ፡ ደግሞ ፡ ይህን ፡ ሥራቸውን ፡ በደንብ ፡ ለማካሄድ ፡ ተገቢው ፡ ቦታና ፡ ሥልጣን ፡ አልተሰጣቸውም ። እነኝህ ፡ ኀብሮች ፡ የአቋማቸውን ፡ ፖሊሲና ፡ ዐላማ ፡ በገንዘብ ፡ በሰው ፡ ኃይል ፡ በዕቃ ፡ በኩል ፡ ዕቅድን ፡ ለማስፈጸም ፡ ይኖሩታል ፡ የተባሉትም ፡ ምንጮች ፡ ጠንቅቀው ፡ በሙሉ ፡ ማወቅ ፡ አለባቸው ። ደግሞ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ የመንግሥቱ ፡ የልማት ፡ ፖሊሲ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የተወ ሰኑትን ፡ ጉዳዮች ፡ ጠንቅቆ ፡ ማወቅና ፡ እንዲሁም ፡ ከዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ ማድረግ ፡ አለባቸው ። እያንዳንዱ ፡ ኀብረት ፡ በቀጠናው ፡ የሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ አማካይነት ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትና ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አማካሪ ፡ ያለበትን ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ፖሊሲና ፡ (ቋሚ ፡ መምሪያ) ፡ ዐላማ ፡ ሲያቀርብ ፡ በተጨማሪ ፡ የዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሠንጠ ረዥ ፡ ዝግጅትን ፡ የሚወስኑትን ፡ ነገሮች ፡ መጥቀስ ፡ አለበት ።

እነዚህም ፡ ኀብሮች ፡ የልማት ፡ ኀብሮች ፡ ተብለው ፡ መሰየም ፡ አለባቸው ። ተግባራቸውም ፡ ዕቅዶችን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዦችን ፡ ውጥኖችን ፡ እንዲሁም ፡ የዕቅዶችን ፡ ማውጣት ፡ ሥራ ፡ ስለሚጨምር ፡ ይህ ፡ ስም ፡ በትክክል ፡ ይገልጻ ቸዋል ። የልማት ፡ ኀብሮች ፡ በመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ጠቅላይ ፡ ሹም ፡ ኀላፊነት ፡ ሥር ፡ የሚገኙ ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አንድ ፡ ቁራሽ ፡ ክፍል ፡ መሆናቸው ፡ እንዲ ታወቅ ፡ ያስፈልጋል ። እንዲሁም ፡ ከሌሎቹ ፡ የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ የተለየ ፡ ግንኙነት ፡ እንዳላቸው ፡ መታወቅ ፡ አለበት ። ከተግባራቸው ፡ አንዱ ፡ የዕቅድ ፡ አካላዊ ፡ ክፍሎች ፡ ከክፍሎቻቸው ፡ ጋር ፡ ከፍተኛ ፡ መተባበር ፡ ማድረ ጋቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

### ዕቅድ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ ርዳታን ፡ የሚያበረክቱ ፡ (ቴክኒካል) ፡ ኪነታዊ ፡ ክፍሎች ።

### ፩. <u>የጠቅላይ ፡ እስታትስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ።</u>

እምነት ፡ የሚጣልበት ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ዝርዝር ፡ ማቅረብ ፡ ለዕቅድና ፡ ለሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ (ፕሮግራም) ፡ ዝግጅትና ፡ በየጊዜው ፡ ለሚደረገው ፡ የዕ

31. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፲፺፯ ፡ ተጠቅሷል ።

ቅድና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ጥቅም ፡ ይሰጣል ። እንደዚሁ ፡ ዓይነቶቹ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ዝርዝሮች ፡ ከዚህ ፡ ቀደም ፡ ለመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ ለግል ፡ ድርጅቶች ፡ ተከፋፍለው ፡ ነበር ። የንግድና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴርና ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክ ፡ እነዚህን ፡ ዝርዝሮች ፡ ለማጠቃለል ፡ ለማስተባበርና ፡ በመልክ ፡ በመልክ ፡ ለመከፋፈል ፡ ሞክረው ፡ ነበር ።

የጠቅላይ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ተቋቁሞ ፡ ለ፲፱፻፶፫ ፡ ዓ. ም. ራሱን ፡ የቻለ ፡ ባጀት ፡ ተሰጠው ። ከጥር ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ. ም. ዠምሮ ፡ ግን ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ ተደረበ ። ተግባሩም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የሚገኙትን ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ክፍሎች ፡ ማስተባበርና ፡ ደንበኛ ፡ የብሔራዊ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ አገልግሎትን ፡ አመሠራረት ፡ ማቀድ ፡ ነው ። ከየሚኒስቴሮች ፡ ተወጣጥቶ ፡ ባ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. የተቋቋመው ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ኮሚቴ ፡ ለዚህ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አማካሪ ፡ ነው ።

ከየሚኒስቴሮች ፡ የተወጣጣው ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ኮሚቴ ፡ በሰኔ ፡ ወር ፡ ፲፱፻፶፪ ፡ ዓ. ም. ለአምስት ፡ ዓመት ፡ (፲፱፻፶፭—፲፱፻፶፱)፡ ያዘጋጀው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ያዲስ ፡ እስታቲስቲክስን ፡ አሰባሰብ ፡ ቅደም ፡ ተከተልና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ከማውጣቱም ፡ በላይ ፡ የእስታቲስቲክስ ፡ አገልግሎት ፡ የሚስፋፋበትንና ፡ የሚያድግበትን ፡ ዘዴ ፡ አደራጅቶአል ። እንዲሁም ፡ ለብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ነገሮች ፡ በመመልከት ፡ ያዲስ ፡ እስቲታቲክስ ፡ አገልግሎት ፡ አቋቋምን ፡ ቅደም ፡ ተከተልና ፡ የጠቅላይ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚያድግበትን ፡ ዘዴ ፡ አደራጅቶአል ። ይህ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለስታቲስቲክስ ፡ እድገት ፡ መመሪያ ፡ ጽሑፍ ፡ ሆኖአል ።

የጠቅላይ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ከተቋቋመ ፡ ወዲህ ፡ ብዙ ፡ መሻሻል ፡ ተደርጎአል ። ሆኖም ፤ የተፈጸመው ፡ ሥራ ፡ የተቆራረጠና ፡ በባጀት ፡ በኩልና ፡ በየጊዜው ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ በሚያጋጥመው ፡ ችግር ፡ ምክንያት ፡ ተለዋዋጭ ፡ ነበር ፡ እንጂ ፤ ደንበኛ ፡ የልማት ፡ ዕቅድን ፡ የተከተለ ፡ አልነበረም ።

በደንብ ፡ ባልተባበሩት ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወኪሎች ፡ በኩል ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መሻሻል ፡ ተደርጎአል ። ልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችና ፡ ድርጅቶች ፡ በኅብረት ፡ ሳይሆን ፡ በነፍስ ፡ ወከፍ ፡ በሚያደርጉት ፡ ጥረት ፡ ትንሽ ፡ መሻሻል ፡ ተደርጎአል ። በልዩ ፡ ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሥር ፡ የሚገኙት ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ክፍሎች ፡ የሚፈጽሟቸው ፡ ተግባሮች ፡ ተስፋፍተውና ፡ ተስተባብረው ፡ ተፈላጊ ፡ የሆነውን ፡ የስታቲስቲክስ ፡ (ዝርዝር) ፡ ዓይነትና ፡ ብዛት ፡ እንዲያስገኙ ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

በእስታቲስቲክስ ፡ አገልግሎት ፡ ውስጥ ፡ ያለው ፡ ሌላ ፡ አንድ ፡ ጉድለት ፡ ደግሞ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ በቂ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ክፍሎች ፡ አለመኖራቸው ፡ ነው ። የእርሻ ፡ ሚኒስቴር ፡ የኢትዮጵያ ፡ የንግድ ፡ ባንክ ፡ የጉምሩክ ፡ መሥሪያ ፡ ቤትና ፡ የንግድንና ፡ ኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስቴር ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ የሚያቀርቡ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤቶች ፡ ስለአሉአቸው ፤ እነዚህ ፡ ተስፋፍተው ፡ ለዋና ፡ ዋና ፡ የመንግሥት ፡ መሥራሪያ ፡ ቤቶች ፡ በነሱም ፡ በኩል ፡ ለጠቅላይ ፡ እስታቲስክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚቀርብ ፡ የማያቋርጥና ፡ የተስተካከለ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ የሚያቀርቡ ፡ ክፍሎች ፡ መሆን ፡ አለባቸው ።

በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ. ም. የስታቲስክስን ፡ አገልግሎት ፡ በደንብ ፡ ለማደራጀት ፡ የተዘጋጀው ፡ የጠቅላይ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ የጠ

ቅላይ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በሕግ ፡ እንዲቋቋምና ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ (ማለት ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ክፍል) ፡ ፕሬዚዳንት ፡ በሆኑት ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተጠያቂ ፡ እንዲሆን ፡ ከማዘዙም ፡ ሌላ ፡ የዚህኑ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ተግ ባርና ፡ ሥልጣን ፡ ያትታል ።

ይህ ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅና ፡ የብሔራዊ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ዐዋጅ ፡ ረቂቅ ፡ ለን ጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግዛት ፡ ለስታቲስቲክስ ፡ አገልግሎት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ሕጋዊ ፡ መመሪያ ፡ መደቦች ፡ አቋቁመዋል ።

ይህ ፡ የቀረበው ፡ ሕግ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ አገልግሎት ፡ ባንድ ፡ ሥልጣን ፡ ሥር ፡ እንዳይሆን ፡ ከማድረጉ ፡ ሌላ ፡ የጠቅላይ ፡ ስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትን ፡ የበላይ ፡ አስተባባሪና ፡ ተቆጣጣሪ ፡ ባለሥልጣን ፡ ያደርገዋል ። በተጨማሪም ፡ ክፍሎች ፡ እርስ ፡ በርሳቸው ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ የሚተባበሩበትን ፡ ዘዴ ፡ መሥርቷል። ደግሞም ፡ በማነኛውም ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ፖሊሲ ፡ (ቋሚ ፡ መመሪያ) ፡ ረገድ ፡ ጠቅላይ ፡ የስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤትን ፡ በቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በኩል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ አማካሪ ፡ እንዲሆን ፡ አድርጎታል ።

የጠቅላይ ፡ እስታቲስቲክስ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ የዝርዝ ዝሮች ፡ ምንጭ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ በመላ ፡ ኀላፊ ፡ በሚሆን ፡ ባንድ ፡ ሚኒስትር ፡ ዴታ ፡ ቍጥጥር ፡ ሥር ፡ መሆን ፡ አለበት ።

<u>የቴክኒክ ፡ (ኪነታዊ) ፡ ድርጅት ።</u>

የቴክኒክ ፡ ድርጅት ፡ በቴክኒክ ፡ ድርጅት ፡ ትእዛዝ ፡ መሠረት ፡ ባ፲፱፻፶፯ (፲፱፻፷፭) ዓ. ም. ተቋቁሞ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ አካላዊ ፡ ክፍል ፡ ሆኖ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ ቀጥታ ፡ ተቆጣ ጣሪነት ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራ ፡ መሆኑ ፡ ተገልጾአል ።[32]

የድርጅቱ ፡ ተግባሮችና ፡ ሥራዎች ፡ በትእዛዙ ፡ ውስጥ ፡ ከዚህ ፡ እንደሚ ከተለው ፡ ተዘርዝረዋል ።

(፩) በጸደቀው ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ መሠረት ፤ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጥያቄና ፡ ተገቢውን ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በማማከር ፡ የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ ጥናትን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋዋል ፡ መከታተልና ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ልማት ፡ ውጥኖችና ፡ በልማት ፡ ዕቅዶች ፡ መሠረት ፡ የተቋቋሙትን ፡ የሥራ ፡ ጅምሮች ፡ ማካሄድ ።

(፪) የነዚህን ፡ ዕቅዶች ፡ ዝግጅትና ፡ በተገቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሚኒ ስቴሮች ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ እንዲጸድቁ ፡ መቅረባቸውን ፡ መከታተል ፡ እንዲሁም ፡ በሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤ ፡ ጥያቄና ፡ ከተገቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሚኒስቴሮች ፡ በመመካከር ፡ ማነኛውንም ፡ አስፈ ላጊውን ፡ ንድፍ ፡ ዕቅድ ፡ የሥራ ፡ ዝርዝሮች ፡ ሥዕሎች ፡ ሌላም ፡ ለተ ጫራቾች ፡ መጠየቂያና ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ አገልግሎት ፡ መሥሪያና ፡ ማቋ ቋሚያ ፡ የሚያስፈልጉትን ፡ ማዘጋጀት ፡ ወይም ፡ እንዲዘጋጁ ፡ ማድረግ ።

---

32. ሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ፩ኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ገጽ ፡ ፫፻፷፫ ።

(፫) በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጥያቄና ፡ ከተገቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ወይም ፡ ሚኒስቴሮች ፡ ጋር ፡ በመመካከር ፡—

ሀ) የመሐንዲስ ፡ ሥራዎችን ፡ ተጫራቾች ፡ መጠየቅና ፡ ስለ ፡ ውሉ ፡ አፈጻጸም ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፤

ለ) ውሎችን ፡ ማዘጋጀትና ፡ ስለ ፡ አፈጻጸማቸው ፡ ያለውን ፡ ማነኛውንም ፡ ስምምነት ፡ ማድረግ ፤

ሐ) ሥራዎችን ፡ መቆጣጠርና ፡ በውሉ ፡ መሠረት ፡ ለተቋራጮች ፡ ገንዘቡ ፡ እንዲከፈላቸው ፡ ማድረግ ፤

መ) ለተቋቋሙት ፡ ኢንዱስትሪዎች ፡ ብቁ ፡ የሆኑ ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ ስለ መቅጠር ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ።

በግል ፡ ሀብት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ለሚካሄዱት ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ውጥኖች ፡ ሁሉ ፡ አገልግሎትን ፡ የሚያበረክተው ፡ ይህ ፡ ድርጅት ፡ ማንኛመንም ፡ ሥራዎቹን ፡ በቀጥታ ፡ በራሱ ፡ ሠራተኞች ፡ በኩል ፡ ወይም ፡ ራሳቸውን ፡ በቻሉ ፡ ዐዋቂዎች ፡ አገልግሎት ፡ በመጠቀም ፡ እንዲያካሂድ ፡ ሥልጣን ፡ ተሰጥቶታል ። ለድርጅቱ ፡ በሚሰጡት ፡ ውጥኖች ፡ በኩል ፡ እንዲያገለግሉ ፡ ሲባል ፡ የግል ፡ የአርችቴክትና ፡ የመሐንዲስ ፡ ሥራ ፡ አማካሪ ፡ ድርጅቶችም ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ እንዳሉ ፡ እንዲቆዩ ፡ ተደርጓል ።

፩ኛ/ በዕቅድ ፡ በኩል ፡ ስለሚመጡት ፡ የፖሊሲና ፡ (ቋሚ ፡ መመሪያ) የተጨበጡ ፡ ነገሮች ፡ ፪ኛ/ ውጥኖችንና ፡ ሌሎች ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማቋቋምና ፡ ለማካሄድ ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ የሚሰጡት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤና ፡ የተገቢው ፡ ሚኒስቴር ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ ይህ ፡ ድርጅት ፡ ስለ ፡ ሥራው ፡ ሁልጊዜ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ማስታወቅ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ በቀጥታ ፡ ውጥኑ ፡ ከሚጠቅሰው ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ የቅርብ ፡ ግንኙነት ፡ እያደረገ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆነ ፡ ዜጊ ፡ ቴክኒሽያኖችና ፡ (ዕደ ፡ ጠቢቦች) ልዩ ፡ ዐዋቂዎችን ፡ የሚይዝ ፡ አማካሪ ፡ ጉባኤ ፡ ማቋቋም ፡ አለበት ። የአማካሪ ፡ ጉባኤ ፡ አባሎችን ፡ ከሌሎች ፡ ድርጅቶች ፡ በፈቃድ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ።

ይህ ፡ ድርጅት ፡ ገና ፡ በደንብ ፡ አልተቋቋመም ። አገልግሎቱም ፡ ለኢኮኖሚና ፡ ለማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ (ሰንጠረዥ) ጠቃሚ ፡ መሆኑ ፡ ገና ፡ አልተረጋገጠም ፤ በሥራ ፡ ላይ ፡ ሊውል ፡ የሚችል ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለማውጣት ፡ በቂ ፡ ጥናት ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። የዚህን ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ ከሌሎች ፡ የዕቅድና ፡ የልማትን ፡ ሥራ ፡ ከሚያካሂዱ ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ ለማስተባበር ፡ ይህ ፡ ድርጅት ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተጠያቂ ፡ እንዲሆንና ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ለማነኛውም ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ኀላፊ ፡ በሚሆን ፡ አንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ደኤታ ፡ ቍጥጥር ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ መደረግ ፡ አለበት ።

፫/ <u>የልማት ፡ ገንዘብ ።</u>

የልማት ፡ ገንዘብ ፡ የልማት ፡ ውጥኖችን ፡ ለማካሄጃ ፡ ከተለየ ፡ የመንግሥት ፡ ገንዘብ ፡ ወጪ ፡ ሆኖ ፡ የተቀመጠ ፡ ገንዘብ ፡ ነው ። ይህ ፡ ገንዘብ ፡ በዓመቱ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ መሠረት ፡ ለጸደቁት ፡ ውጥኖች ፡ ይሆናሉ ፡ ተብለው ፡ የተወሰኑትን ፡ ሌሎች ፡ ሀብቶችንም ፡ ለነዚህ ፡ ውጥኖች ፡ እንዲውሉ ፡ ለማድረግ ፡

ይረዳል ። ሆኖም ፡ ፩ኛ/ ይህን ፡ ለልማት ፡ ውጥኖች ፡ የተወሰነውን ፡ ገንዘብ ፡ ፪ኛ/ ውጥኖች ፡ ከተቋቋሙ ፡ በኋላ ፡ ተደጋግመው ፡ ለሚመጡት ፡ ጉዳዮች ፡ ወጪ ፡ ይሆናል ፡ ተብሎ ፡ የተፈቀደውን ፡ ገንዘብ ፡ ፫ኛ/ ለሌሎች ፡ ጉዳዮች ፡ ተመድበው ፡ በድርጅቶችና ፡ በሚኒስቴሮች ፡ እጅ ፡ የሚገኙትን ፡ ሀብቶች ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መንገድ ፡ እንዲከፋፈሉ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ተቆጣጣሪዎች ፡ ሥር ፡ እንዲሆኑና ፡ በተለያዩ ፡ የአስተዳደር ፡ ደንቦች ፡ ሥር ፡ እንዲውሉ ፡ በማድረግ ፡ ችግር ፡ ይፈጥራል ። በዚህ ፡ የልማት ፡ ገንዘብ ፡ ምክንያት ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚውን ፡ ክፍል ፡ ሥልጣን ፡ ይህን ፡ ገንዘብ ፡ በእጅ ፡ ያደረገው ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ክፍል ፡ ወስዶ ፡ ለሥራው ፡ አፈጻጸም ፡ ኀላፊ ፡ ይሆናል ። ለሁለተኛው ፡ የአምስት ፡ ዓመት ፡ ፕላን ፡ (ዕቅድ) መግቢያ ፡ (ማብራሪያ) የሆነው ፡ ጽሑፍ ፡ እንደሚገልጸው ፡ የልማቱ ፡ ገንዘብ ፡ የልማት ፡ ዕቅዶችን ፡ ለማሻሻል ፡ ሲባል ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሥር ፡ ተመድቦአል ።[33] ሆኖም ፡ በተከታታዮቹ ፡ የዓመት ፡ ባጀት ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ገንዘብ ፡ ስላልተጠቀሰ ፡ ውሳኔው ፡ የተለወጠ ፡ ይመስላል ።

## ፬/ ካፒታልን፡(ገንዘብን) በልማት፡ሥራ፡ላይ፡እንዲውል፡የሚያበረታታ፡ኮሚቴ።

ይህ ፡ ኮሚቴ ፡ ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ (፲፱፻፷፫) በወጣው ፡ ድንጋጌ ፡ የተቋቋመ ፡ ሲሆን ፡[34] ዋና ፡ ተግባሩም ፡ የግል ፡ ገንዘብ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ ገንዘባቸውን ፡ (ካፒታላቸውን) በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ለሚችሉ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ድርጅቶች ፡ የቀረጥ ፡ ምሕረትና ፡ ሌላም ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ ሊደረግላቸው ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፤ እንዲሁም ፡ ሌላ ፡ አስፈላጊ ፡ ጥቅምና ፡ መብት ፡ ሊሰጥ ፡ የሚቻልበትን ፡ መንገድ ፡ ማጥናትና ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ ነው ። በድንጋጌው ፡ መግቢያ ፡ እንደተገለጸው ፡ ከውጭ ፡ አገርም ፡ ሆነ ፡ ከአገር ፡ ውስጥ ፡ የሚገኝ ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የዚህ ፡ ዐይነት ፡ ማበራታት ፡ እንዲደረግ ፡ ታስቧል ።

የዚህ ፡ ኮሚቴ ፡ አባሎች ፡ የእርሻ ፡ ሚኒስትር ፡ የንግድና ፡ የኢንዱስትሪ ፡ ሚኒስትር ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ (ወይም ፡ እነሱ ፡ የወከሏቸው ፡ ተጠሪዎች) የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ ባንክ ፡ ገዥና ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ናቸው ።

ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የታቀዱ ፡ የግል ፡ ውጥኖች ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውም ፡ ሚኒስቴር ፡ በሕግ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ ልዩ ፡ አስተያየት ፡ እንዲደያደርግላቸው ፡ የሚያስፈልግ ፡ ሲሆን ፡ ለምርመራ ፡ ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለሚያበረታታው ፡ ኮሚቴ ፡ መቅረብ ፡ አለባቸው ። ኮሚቴውም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚጠቅሰው ፡ ሚኒስቴር ፡ በሕግ ፡ መሠረትና ፡ ለሚኒስቴሩ ፡ በተፈቀደው ፡ ያልተወሰነ ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ ስለ ፡ ውጥኖቹ ፡ ምን ፡ ርምጃ ፡ መውሰድ ፡ እንደሚገባው ፡ ሐሳብ ፡ ያቀርባል ። ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የሚያበረታታው ፡ ኮሚቴ ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ውስጥ ፡ ለማንኛውም ፡ ዕቅድ ፡ ኀላፊ ፡ በሆነ ፡ አንድ ፡ ሚኒስትር ፡ ዴኤታ ፡ ሥር ፡ እንዲሆን ፡ አንድ ፡ ዐይነት ፡ ርምጃ ፡ መወሰድ ፡ አለበት ።

ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የሚያበረታታው ፡ ኮሚቴ ፡ ከተቋቋመ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ስላልሆነው ፡ ለልማት ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ሥራ ፡ የሰጠውን ፡ ጥቅም ፡ ለማመዛዘን ፡ ያስቸግራል ።

---

33. እላይ ፡ የተጠቀሰው ።
34. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቊጥር ፡ 16 ፡ ተጠቅሷል ።

## ፮/ የኢኮኖሚና ፡ (የቴክኒክ) የኪነታዊ ፡ ተራድኦ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ።

አሁን ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ የሚሠራው ፡ የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ ርዳታ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ የተቋቋመው ፡ የቀድሞውን ፡ የቴክኒክ ፡ ርዳታ፡ ኮሚቴና ፡ የኢኮኖሚ ፡ ርዳታ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ለመተካት ፡ ነበር ። ይኸ ፡ ጉባኤ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ እርዳታ ፡ ከሚሰጡ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታትና ፡ ኢንተርናሽናል ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ ስምምነት ፡ ያደርጋል ። ሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤ ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ (በመንግሥት) የተቋቋመ ፡ እንጂ ፡ በተለይ ፡ በሕግ ፡ የታወቀ ፡ አይደለም ።

ሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤ ፡ አሁን ፡ ለጊዜው ፡ የሚሠራው ፡ ከተባበሩት ፡ መንግሥታትና ፡ ከአሜሪካን ፡ መንግሥት ፡ ስለሚመጣው ፡ እርዳታ ፡ ብቻ ፡ ሲሆን ፡ ከሌላ ፡ ምንጮች ፡ የሚመጡት ፡ ርዳታዎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ በተለይ ፡ ጉዳዩ ፡ በሚጠቅሰው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ በኩል ፡ ስምምነት ፡ እንዲደረግባቸው ፡ ትቶአቸዋል ። ሆኖም ፡ የብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ኢንተርናሽናል ፤ የግል ፡ ወይም ፡ የመንግሥት ፡ ከሆኑት ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ አቋሞች ፡ ጋር ፡ ለኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ እርዳታን ፡ በመስጠት ፡ በኩል ፡ ስላለው ፡ ጉዳይ ፡ ስምምነት ፡ የማድረግና ፡ ውሎችን ፡ የመፈረም ፡ ሥልጣን ፡ በተለይ ፡ ለዚህ ፡ ጉባኤ ፡ ተሰጥቶታል ። ዳግም ፡ ጉዳዩ ፡ የሚጠቅሳቸው ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ተጠሪዎች ፡ በንግግሩ ፡ ላይ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ይደነግጋል ። እንዲሁም ፡ ካገር ፡ ውስጥ ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠይቅ ፡ ማነኛውም ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ እርዳታ ፡ ውል ፤ ገንዘቡ ፡ የሚውልበት ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ውጥን ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ኮሚቴ ፡ ለጊዜው ፡ ባጸደቀው ፡ የሥራ ፡ (ፕሮግራም) ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ከሌለና ፡ ሥራው ፡ ይፈጃል ፡ ተብሎ ፡ የታሰበው ፡ ገንዘብ ፡ በዚሁ ፡ ሰንጠረዥ ፡ የተገለጸ ፡ ካልሆነ ፡ በስተቀር ፡ እንዳይፈረም ፡ ትእዛዙ ፡ ይከለክላል ።

ዕቅድን ፡ በደንብ ፡ ለማውጣት ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ የሚገኙት ፡ እርዳታዎች ፡ በመላ ፡ ከልማት ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጋር ፡ እንዲስተባበሩ ፡ ያስፈልጋል ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ውጭ ፡ አገር ፡ ርዳታዎች ፡ ሁሉ ፡ ስምምነት ፡ የማድረጉ ፡ ኀላፊነት ፡ እንደዚህ ፡ የሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ላሉ ፡ ድርጅቶች ፡ እንዲሰጥ ፡ በጣም ፡ አስፈላጊ ፡ ነው ። በሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤና ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ በየጊዜው ፡ ብዙ ፡ የሐሳብ ፡ መለዋወጥ ፡ ስለሚያስፈልግና ፡ ሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤም ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ ከፍተኛ ፡ ተግባር ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ስንመለከት ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሥር ፡ ከሚሆን ፡ ይልቅ ፡ ከጠቅላይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጋር ፡ ተደርቦ ፡ ለማነኛውም ፡ የዕቅድ ፡ ኀላፊ ፡ በሆነ ፡ አንድ ፡ ሚኒስትር ፡ ደኤታ ፡ ቊጥጥር ፡ ሥር ፡ መሆን ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ ይህ ፡ የሥራ ፡ መሪው ፡ ጉባኤ ፡ በሕግ ፡ ቢቋቋምና ፡ ሥልጣኑና ፡ ተግባሩም ፡ በሕጋዊ ፡ ጽሑፍ ፡ ቢወጣ ፡ መልካም ፡ ነው ።

በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ መሠረት ፡ የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ እርዳታ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ አዋዋል ፡ የልማት ፡ ዕቅዶችንና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦችን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ ከሚደረገው ፡ ቊጥጥርና ፡ ተከታትሎ ፡ ማስፈጸም ፡ ሥራ ፡ ጋር ፡ የተያያዘ ፡ ይሆናል ። [35]

---

35. እታች ፡ ምዕራፍ ፡ ፮ ፡ ተመልከት ።

## ፭/ የአምስት ፣ ዓመት ፣ ዕቅዶች ።

የአምስት ፣ ዓመት ፣ ዕቅድን ፣ ግብ ፣ (ዓላማ) አወሳሰን ፣ በመዠመሪያ ፣ ፖለቲካን ፣ የሚመለከት ፣ ነገር ፣ ነው ፤ ግቡም ፣ ሲወሰን ፣ ከኢኮኖሚና ፣ ከማኅበራዊ ፣ ኑሮ ፣ ጉዳዮች ፣ ሌላ ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥቱን ፣ መንግሥት ፣ ቋሚ ፣ መመሪያ ፣ (ፖሊሲ) ማመዛዘን ፣ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፣ የተነሣ ፣ ለያንዳንዱ ፣ የአምስት ፣ ዓመት ፣ ዕቅድ ፣ መነሻ ፣ የሚሆነውን ፣ ቋሚ ፣ መመሪያ ፣ ማጽደቅና ፣ ዕቅዱንም ፣ በሥራ ፣ ላይ ፣ ማዋል ፣ የሚኒስትሮች ፣ ጉባኤና ፣ የንጉሠ ፣ ነገሥቱ ፣ ኀላፊነት ፣ መሆን ፣ አለበት ። የዚህ ፣ ዓይነቱ ፣ የኅብረ ፣ ሰብ ፣ ኢኮኖሚ ፣ ጉዳይ ፣ እንጂ ፣ የሕግ ፣ ጉዳይ ፣ መሆን ፣ ስለማያስፈልገው ፣ በፓርላማ ፣ ማጽደቅ ፣ ተገቢ ፣ አይደለም ። ዕቅዱ ፣ ሊፈጽማቸው ፣ ያቀደውን ፣ ዐላማና ፣ በዕቅዱ ፣ በኩል ፣ ያሉትን ፣ ጉዳዮችና ፣ ሐሳቦች ፣ ለፓርላማ ፣ በሙሉ ፣ ማስታወቅ ፣ እንጂ ፣ ዕቅዱን ፣ እንዲያጸድቅ ፣ ወይም ፣ በሕግ ፣ ደንግጎ ፣ እንዲያወጣ ፣ መጠየቅ ፣ አያስፈልግም ።

አሁን ፣ በሚሠራበት ፣ ደንብና ፣ በብሔራዊ ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ አመራር ፣ የትእዛዝ ፣ ረቂቅ ፣ መሠረት ፣ የአምስት ፣ ዓመት ፣ ዕቅዶችን ፣ በመጨረሻ ፣ የሚያጸድቀው ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ መሪ ፣ ጉባኤ ፣ ነው ። እነዚህ ፣ ዕቅዶች ፣ በንጉሠ ፣ ነገሥቱና ፣ በሚኒስትሮች ፣ ጉባኤ ፣ መጠናታቸው ፣ ተገቢ ፣ መስሎ ፣ ቢታይም ፣ ቅሉ ፣ አሁን ፣ የሚሠራበትም ፣ መንገድ ፣ የነዚህን ፣ ዕቅዶች ፣ ፖለቲካዊ ፣ ጉዳይ ፣ በሰፊው ፣ ይፈጽማል ።

በያንዳንዱ ፣ የአምስት ፣ ዓመት ፣ ዕቅድ ፣ ውስጥ ፣ የሚጠቃለሉትን ፣ ቋሚ ፣ መመሪያዎችና ፣ (ፖሊሲዎች) ግቦች ፣ ማጥናት ፣ ባሁኑ ፣ ጊዜ ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ መሪ ጉባኤ ፣ ተግባር ፣ ነው ። ሆኖም ፣ በብሔራዊ ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ አመራር ፣ የትእዛዝ ፣ ረቂቅ ፣ መሠረት ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ ድርጅቶች ፣ የሚመሩባቸውን ፣ የመንግሥቱን ፣ ቋሚ ፣ መመሪያዎች ፣ መተርጐም ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ አጥኚ ፣ ጉባኤ ፣ ተግባር ፣ ነው ። ቀደም ፣ ብሎ ፣ እንደተብራራው [36] ፣ እነዚህ ፣ ቋሚ ፣ መመሪያዎች ፣ መዠመሪያ ፣ በዕቅድ ፣ ጽሕፈት ፣ ቤት ፣ የምርመራና ፣ ጥናት ፣ ክፍል ፣ ከተወሰኑ ፣ በኋላ ፣ እንዲጸድቁ ፣ ለዕቅድ ፣ ሥራ ፣ አጥኚ ፣ ጉባኤ ፣ መቅረብ ፣ አለባቸው ።

## ፮/ የአካባቢዎች ፣ የሥራ ፣ ሰንጠረዥና ፣ ከብሔራዊ ፣ ዕቅድ ፣ ጋር ፣ ያላቸው ፣ መተባበር ።

በኢትዮጵያ ፣ በዘጠና ፣ ስምንት ፣ አውራጃዎች ፣ የተከፋፈሉ ፣ ዐሥራ ፣ አራት ፣ ጠቅላይ ፣ ግዛቶች ፣ አሉ ። የጠቅላይ ፣ ግዛቶችና ፣ የአውራጃዎች ፣ አስተዳደር ፣ ከዋናው ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ መንግሥት ፣ አስተዳደር ፣ ጋር ፣ የተያያዘ ፣ ስለሆነ ፣ ጠቅላይ ፣ ግዛቶችና ፣ አውራጃዎች ፣ ራሱን ፣ የቻለ ፣ የግል ፣ አስተዳደር ፣ የላቸውም። ባሁኑ ፣ ጊዜ ፣ አውራጃዎች ፣ የተወሰነ ፣ የግል ፣ አስተዳደር ፣ ሥልጣን ፣ እንዲሰጣቸው ፣ ሐሳብ ፣ ቀርቦአል ። ይህ ፣ ሐሳብ ፣ የጸደቀ ፣ እንደሆነ ፣ የመንግሥት ፣ መሥሪያ ፣ ቤቶችና ፣ የዕቅድ ፣ ሥራ ፣ ድርጅቶች ፣ ከነዚህ ፣ አውራጃዎች ፣ ጋር ፣ ያላቸውን ፣ ግንኙነት ፣ በጣም ፣ ይለውጠዋል ። ከዚህ ፣ በታች ፣ የሚቀጥለው ፣ ማብራሪያ ፣ የተመሠረተው ፣ አሁን ፣ ባለው ፣ የአስተዳደር ፣ ሁኔታ ፣ ላይ ፣ ነው ።

36. እላይ ፣ ምዕራፍ ፣ ፬-(፫) ፣ ተመልከት ።

እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ ምንም ፡ ዓይነት ፡ የአካባቢ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ አል
ነበሩም ። እንዲሁም ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛትና ፡ በአውራጃዎች ፡ ደረጃ ፡ የቀጠና ፡
ዕቅዶች ፡ ማስተባበሪያ ፡ ዘዴ ፡ አልነበረም ። ዕቅድና ፡ ልማት ፡ የመንግሥት ፡ መሥ
ሪያ ፡ ቤቶች ፡ በቀጠናቸው ፡ ውስጥ ፡ ካሉ ፡ የግል ፡ ድርጅቶች ፡ ጋር ፡ በመማከር ፡
መፈጸም ፡ የሚገባቸው ፡ ተግባሮች ፡ ናቸው ፤ ተብለው ፡ ስለሚታሰቡ ፡ የጠቅላይ ፡
ግዛት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ሥልጣን ፡ አልተሰ
ጣቸውም ። የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ባለሥልጣኖች ፡ እንደመሆናቸው ፡
መጠን ፡ ዕቅዱ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቱን ፡ ስለሚመለከትበት ፡ ጉዳይ ፡ ሐሳብ ፡ እንዲያ
ቀርቡ ፡ ይጠይቁ ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡ ስለ ፡ ጠቅላላው ፡ ዕቅድ ፡ ወይም ፡ በአካባ
ቢው ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሥራዎች ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ምንም ፡ ውሳኔ ፡ ሊያደርጉ ፡
አይችሉም ።

በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ በኩል ፡ ከሚገኘው ፡ መረጃ ፡ ሌላ ፡ በን
ጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ከማናቸውም ፡ የልማት ፡ ሥራ
ዎችንና ፡ ውጥኖችን ፡ ከሚያካሂዱ ፡ ድርጅቶች ፡ የሚመጡትን ፡ ሐሳቦችና ፡ አስተ
ያየቶች ፡ ሁሉ ፡ ማጥናትና ፡ ማመዛዘን ፡ ያስፈልጋል ። ስለዚህ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ
ዎች ፡ በዕቅድ ፡ አቋም ፡ ውስጥ ፡ የታወቀ ፡ ቦታ ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ያስፈልጋል ።
ሆኖም ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይነታቸው ፡ በአንድ ፡ ጊዜ ፡ ሳይሆን ፡ ቀስ ፡ በቀስ ፡
እያደገ ፡ የሚሄድ ፡ ቢሆን ፡ መልካም ፡ ሳይሆን ፡ አይቀርም ።

በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ ጠቅላይ ፡
ገዥዎችና ፡ ሌሎችም ፡ የአውራጃና ፡ የቀበሌ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በዕቅድና ፡ በል
ማት ፡ ሥራዎች ፡ ውስጥ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ እንዲያደርግ ፡ የዕቅድና ፡ ሥራ ፡
አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ታዟል ። የሀገሪቱ ፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ ቀበሌዎች ፡ እንደራሴዎችን ፡
በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ተካፋይ ፡ እንዲሆኑ ፡ የሚያደርግ ፡ ተጨማሪ ፡ ሕግ ፡ መውጣት ፡
አለበት ። ሆኖም ፡ እንደራሴዎችን ፡ አሁኑኑ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ውስጥ ፡ በጣም ፡
እንዲገቡ ፡ ማድረግ ፡ ጊዜው ፡ ስለማይፈቅድ ፡ መቸኰል ፡ ይሆናል ።

የጠቅላይ ፡ ገዥው ፡ ሥራ ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙትን ፡ የልዩ ፡
ልዩ ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ የሥራ ፡ (ፕሮግራም) ሰንጠረዥ ፡ ማስ
ተባበርን ፤ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሚገኙት ፡ ውጥኖች ፡ የአፈጻጸማቸውን ፡
ቅደም ፡ ተከተል ፡ ማውጣትን ፤ ሥራው ፡ በሚካሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ተከታትሎ ፡ የሚያ
ጋጥሙትን ፡ ችግሮች ፡ ማመልከትና ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ወኪሎ
ችን ፡ ተገቢ ፡ የርዳታ ፡ ጥያቄ ፡ መደገፍ ፤ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶችን ፡ ስለ ፡
ቀበሌው ፡ ሁኔታ ፡ አቋሞች ፡ ልማዶችና ፡ እምነቶች ፡ ማስረዳትን ፤ ለወደፊት ፡
ለሚደረገው ፡ መሻሻል ፡ ቅደም ፡ ተከተሎችን ፡ ማሳሰብና ፡ ሥራውን ፡ ለማካሄድ ፡
ምን ፡ ዐይነት ፡ ተጨማሪ ፡ ርዳታ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ መመልከትን ፡ ይጨምራል ።

፫/ <u>ለአንዳንድ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ቅርንጫፎች ፡ የሚወጣ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ</u> ።

በደንብ ፡ ቢሠሩም ፡ ባይሠሩም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡
የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ እንዲኖሩ ፡ ሕግ ፡ ያዛል ። ነገር ፡ ግን ፡ የኢኮኖሚ ፡ ቀጠናዎ
ችን ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለማስተባበር ፡ የወጣ ፡ ምንም ፡ ሕግ ፡ የለም ። በአን
ዳንድ ፡ ቦታ ፡ ቀጠናውን ፡ በመላ ፡ አንድ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሲሸፍን ፡ በሌላው ፡ ቦታ ፡
ደግሞ ፡ በብዙ ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ሥር ፡ ተከፋፍሎ ፡ ይገኛል ። ለምሳሌ ፡ በማ
መላለሻና ፡ በመገናኛ ፡ በኩል ፡ ተመዛዛኝ ፡ ልማት ፡ ለማስገኘት ፡ የሥራና ፡ የመ
ገናኛ ፡ ሚኒስቴርን ፡ የፖስታ ፡ ቴሌፎንና ፡ ቴሌግራፍ ፡ ሚኒስቴርን ፡ የኢትዮጵያ ፡

ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ አውራ ፡ ጉዳና ፡ ባለሥልጣንን ፡ የኢትዮጵያ ፡ አየር ፡ መንገድን ፡ ውጥኖች ፡ ሁሉ ፡ ማስተባበሪያ ፡ ፈሊጥ ፡ እንዲገኝለት ፡ ያስፈልጋል ።

አሁን ፡ የተቋቋሙት ፡ ቋሚ ፡ የሥራ ፡ አጥኚ ፡ ኮሚቴዎች ፡ ማለት ፡ የዕቅድና ፡ ገንዘብን ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ የሚያበረታታው ፡ ኮሚቴ ፡ የገንዘብና ፡ የብድር ፡ ኮሚቴ ፡ የንግድ ፡ ኮሚቴ ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ እድገት ፡ ኮሚቴ ፡ የመሬት ፡ ይዞታን ፡ የሚያሻሽልና ፡ ሕዝብን ፡ የሚያሰፍር ፡ ኮሚቴና ፡ ሕግን ፡ የሚያወጡት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ አባሎች ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ ብዙዎችን ፡ የኢኮኖሚ ፡ ቀጠናዎች ፡ ይሸፍናሉ ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፡ ለያንዳንዱ ፡ ከፍተኛ ፡ የኢኮኖሚ ፡ ቀጠና ፡ የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤና ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ደግሞ ፡ ተመሳሳዩን ፡ የቀጠና ፡ ንዑስ ፡ ክፍል ፡ ማቋቋም ፡ ያስፈልጋል ። እነዚህም ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ በቀጠናዎቻቸው ፡ ውስጥ ፡ ያሉትን ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዦች ፡ በማስተባበር ፡ የቀጠናው ፡ ልማት ፡ በመላ ፡ የተመዛዘነ ፡ እንዲሆን ፡ ያደርጋሉ ።

## ፩/ ዕቅድን ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ ለማዋል ፡ የሚወጡ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዦች ።

የማካሄጃው ፡ ባጀት ፡ ከተወሰነ ፡ በኋላ ፡ ለብዙ ፡ ወራት ፡ ያላለቀ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዥ ፡ ፍጹም ፡ ከንቱ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ለሁለቱም ፡ ለባጀትና ፡ ለዕቅድ ፡ የተያያዘ ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዥ ፡ ያስፈልጋል ። የብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ እያንዳንዱ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ደረጃ ፡ የሚፈጸምበትን ፡ ጊዜ ፡ ጭምር ፡ የያዘ ፡ የተባበረ ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዥ ፡ እንዲሠራና ፡ የባጀት ፡ ግምትም ፡ እንዲያዘጋጅ ፡ ያዘዋል ። እነዚህን ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዦች ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በጥብቅ ፡ በሥራ ፡ ላይ ፡ መዋላቸውንና ፡ መፈጸማቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ አለበት ። እንዲሁም ፡ በነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፡ ታትመው ፡ መውጣት ፡ አለባቸው ። እነዚህ ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዦች ፡ በሚዘጋጁበት ፡ ጊዜ ፡ ችግር ፡ እንደሚያጋጥም ፡ የማይጠረጠር ፡ ነው ። ይህም ፡ የሚሆነው ፡ የመዠመሪያው ፡ ዕቅድ ፡ ከባጀት ፡ ማውጣት ፡ ዝግጅት ፡ በፊት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ መዘጋጀት ፡ ስለሚያስፈልገውና ፡ ቋሚ ፡ ለሚሆኑ ፡ ነገሮች ፡ (ካፒታል) የሚደረገው ፡ ወጪ ፡ ተደጋግመው ፡ ለሚመጡት ፡ ነገሮች ፡ ከሚደረገው ፡ ወጪ ፡ ጋር ፡ ተቀናብሮ ፡ ጠቅላላው ፡ ያለቀለት ፡ ባጀት ፡ የባጀት ፡ ዓመት ፡ ከሚዠመርበት ፡ ጊዜ ፡ ትንሽ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ወይንም ፡ ወዲያውኑ ፡ መወሰን ፡ ስለሚያስፈልገው ፡ ነው ። (አሁን ፡ የሚሠራበት ፡ ሕግ ፡ ባጀት ፡ ዓመቱ ፡ ከመዠመሩ ፡ በፊት ፡ መጽደቅ ፡ አለበት ፡ ይላል) ።

የዕቅድ ፡ አወጣጥ ፡ ሥራ ፡ የሚጀመረው ፡ በአምስቱ ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ መሠረትና ፡ ስለ ፡ ዕቅዱ ፡ በጠቅላላው ፡ ባለፈው ፡ ዓመት ፡ የሥራ ፡ ፕሮግራም ፡ ላይ ፡ የተሰጡትን ፡ ጊዜያዊ ፡ መግለጫዎች ፡ በመመልከትና ፡ ያለፈውን ፡ ዓመት ፡ የሥራ ስንጠረዥ ፡ አፈጻጸም ፡ አይቶ ፡ ግቦችን ፡ በመወሰን ፡ ነው ። ይህ ፡ የሚሠራው ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ ክፍል ፡ ሲሆን ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ መግለጫ ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሹም ፡ ከታየ ፡ በኋላ ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ መቅረብ ፡ አለበት ።

ዕቅዱ ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የቀጠና ፡ ክፍሎች ፡ በቀጠናቸው ፡ ላሉት ፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ መመሪያዎችን ፡ ያዘጋጃሉ ። መመሪያዎቹም ፡ የጸደቁትን ፡ ግቦች ፡ የሚገልጹና ፡ በበኩላቸው ፡ ያለውን ፡ የዓመት ፡ የሥራ ፡ ስንጠረዥ ፡ እንዴት ፡ እንደሚያዘጋጅ ፡ የሚያስረዱ ፡ መሆን ፡

አለባቸው ። ይህም ፡ በሚሆንበት ፡ ጊዜ ፡ የቀበሌው ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ የጸደቁትን ፡ ግቦች ፡ ለጠቅላይ ፡ ገዥዎች ፡ ያስታውቁአቸዋል ።

እነዚህን ፡ መመሪያዎች ፡ እንደተቀበሉ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ውስጥ ፡ የሚገኙት ፡ የልማት ፡ ክፍሎች ፡ ከቀጠናው ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ክፍሎች ፡ የሚያስፈልጋቸውን ፡ ርዳታዎች ፡ በመጠየቅና ፡ በአቋማቸው ፡ ውስጥ ፡ ከሚገኙት ፡ ከሌሎቹ ፡ ክፍሎች ፡ ዝርዝሮችን ፡ በመሰብሰብ ፡ ዝግጅት ፡ ይገምራሉ ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ያሉት ፡ የመሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ተጠሪዎች ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥዎች ፡ በቀጠናቸው ፡ ውስጥ ፡ ስላሉት ፡ የልማት ፡ ውጥኖች ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ ጠይቀው ፡ መረዳት ፡ ያስፈልጋልቸዋል ። አንድ ፡ የልማት ፡ ክፍል ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዡንና ፡ የቅደም ፡ ተከተሉን ፡ ዝርዝር ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ሰንጠረዡ ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ ከፍተኛ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ተመርምሮ ፡ ለተገቢው ፡ የቀጠና ፡ ልማት ፡ የሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ይቀርባል ። የሥራ ፡ ሰንጠረዡ ፡ እያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ከጠቅላላው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጋር ፡ ያለውን ፡ ግንኙነት ፡ ከማብራራቱም ፡ ሌላ ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ማካሄጃ ፡ ስለሚሆነው ፡ ገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ ሐሳብ ፡ ያቀርባል ።

የቀጠናው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በቀጠናው ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙት፡ የመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ የተዘጋጀውን ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ አስፈላጊ ፡ በሆን ፡ ጊዜ ፡ ከተመሳሳዩ ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የቀጠና ፡ ክፍል ፡ ርዳታን ፡ እየጠየቀ ፡ በቀረበው ፡ ሐሳብ ፡ ላይ ፡ በመነጋገር ፡ የቀረበውን ፡ ሐሳብ ፡ ጠቃሚነት ፡ ይወስናል ። ከሌላ ፡ ቀጠና ፡ ውስጥ ፡ ካሉት ፡ ውጥኖች ፡ ጋር ፡ ስለ ፡ ተያያዙት፡ ውጥኖች ፡ ከሚጠቅሳቸው ፡ የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤዎች ፡ ጋር ፡ ይነጋገራል ። እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ለቀጠናው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ያወጣል ። ውጥኖቹንም ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ያስቀምጣቸዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዡ ፡ በአስተባባሪና ፡ ተከታትሎ ፡ አስፈጻሚ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ለሚገኘው ፡ የቀጠና ፡ ክፍል ፡ ይተላለፋል ። በዚሁ ፡ ጊዜ ፡ የቀበሌው ፡ የማስተባበሪያና ፡ ተከታትሎ ፡ አስፈጻሚ ፡ ክፍል ፡ የጠቅላይ ፡ ገዥዎች ፡ (ወይም ፡ ተጠሪዎቻቸው) እንዲሰበሰቡና ፡ በጠቅላይ ፡ ግዛታቸው ፡ ውስጥ ፡ በቀረቡት ፡ ውጥኖች ፡ ላይና ፡ በጠቅላላው ፡ ለጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ስለሚያስፈልጉት ፡ ልማቶች ፡ ያላቸውን ፡ አስተያየት ፡ እንዲሰጡ ፡ ያደርጋል ። እነዚህም ፡ አስተያየቶችና ፡ ሐሳቦች ፡ የቀጠናው ፡ ክፍል ፡ እንዲያውቃቸው ፡ ያደርጋል ። የቀጠናው ፡ ክፍሎችም ፡ በተቀበሉት ፡ መረጃ ፡ መሠረት ፡ የቀጠናቸውን ፡ ዕቅዶች ፡ አጠቃለው ፡ ለማስተባበሪያና ፡ ተከታትሎ ፡ ማስፈጸሚያ ፡ ክፍል ፡ ሹም ፡ ያቀርቧቸዋል ። እሱም ፡ አስተባብሮ ፡ የውጥኖችን ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ በመወሰን ፡ የተጠቃለለ ፡ የአንድ ፡ የባጀት ፡ ዓመት ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ያደርገዋል ። በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መፍትሔ ፡ ሊገኝላቸው ፡ ያልቻሉ ፡ ችግሮች ፡ ሁሉ ፡ ለውሳኔ ፡ ወደ ፡ ዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ይተላለፋሉ ።

ቀጥሎም ፡ የተስተባበረው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለጊዜው ፡ እንዲጸድቅ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ይላካል ። እዚህ ፡ ደረጃ ፡ ከደረሰ ፡ በኋላ ፡ ዋናው ፡ አሳሳቢ ፡ ጉዳይ ፡ እያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ተስማሚ ፡ ወይንም ፡ የሚቻል ፡ መሆኑ ፡ ሳይሆን ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ለጊዜው ፡ ለጸደቁት ፡ ውጥኖች ፡ ማካሄጃ ፡ ገንዘብ ፡ መገኘት ፡ አለመገኘቱ ፡ ነው ። ለውጥኖቹ ፡ በመላ ማካሄጃ ፡ ገንዘብ ፡ ያልተገኘ ፡ እንደሆን ፡ ከሥራ ፡ ሰንጠረዡ ፡ የቅደም ፡ ተከተሉን ፡ ዝርዝር ፡ ከሥር ፡ ዠምሮ ፡ አንዳንድ ፡ ውጥኖችን ፡ መቀነስ ፡ ያስፈልጋል ። የሥራ ፡ ሰንጠረዡም፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡

አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ከተመለከታቸው ፡ በኋላ ፡ ከዓመቱ ፡ ባጀት ፡ ጋር ፡ እንዲያመዛዝኑት ፡ ለሚኒስቴሮች ፡ ጉባኤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱና ፡ ለፓርላማ ፡ ይላካል ።[37]

## ፳/ የዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ሕጋዊነት ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፤ ዕቅዶች ፤ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ወይም ፡ ውጥኖች ፡ በራሳቸው ፡ ሕጋዊነት ፡ የላቸውም ። ተደንግጎ ፡ በሚወጣው ፡ በዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ ውስጥ ፡ ለየውጥኑ ፡ የሚያስፈልገው ፡ ገንዘብ ፡ ግምት ፡ ይኖር ፡ ይሆናል ። ለውጥኖች ፡ የሚያስፈልጉ ፡ የኢንተርናስዮናል ፡ ብድሮች ፡ ፓርላማው ፡ ከተስማማባቸው ፡ በኋላ ፡ በውል ፡ ሊገኙ ፡ ይቻላል ። በዚህ ፡ አኳኋን ፡ ውጥኖችና ፡ እንዲሁም ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ በቀጥታ ፡ ሳይሆን ፡ በተዘዋዋሪ ፡ ሕጋዊነት ፡ አላቸው ፡ ሊባል ፡ ይቻላል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሕጋዊነታቸው ፡ አጠራጣሪ ፡ ነው ። ምክንያቱም ፡ በሕግ ፡ የሚታወቁት ፡ ውጥኖቹ ፡ ራሳቸው ፡ ሳይሆኑ ፡ ለነዚህ ፡ የሚመደበው ፡ ባጀት ፡ በመሆኑ ፡ ነው ።

የአምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅዶችና ፡ የረዥም ፡ ዘመን ፡ ውጥኖች ፡ ዝርዝር ፡ አሠራር ፡ የውጥኖችንና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦችን ፡ ሕጋዊነት ፡ ለማሳየት ፡ በቂ ፡ ናቸው ፤ ሊባል ፡ አይቻልም ። ዝርዝር ፡ አሠራርና ፡ የሥራ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ሰንጠረዥ ፡ በሥራ ፡ ክንውን ፡ ጊዜ ፡ ሊለዋወጡ ፡ ስለሚችሉ ፡ በሕግ ፡ መስፈራቸው ፡ ከጠቃሚነቱ ፡ ይልቅ ፡ ጎጂነቱ ፡ ይበልጥ ፡ ይሆናል ። ስለዚህ ፡ ሐሳብ ፡ የቀረበበት ፡ የብሔራዊ ፡ ዕቅድ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ትእዛዝ ፡ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ሕጎች ፡ እንዲወጡ ፡ አይደግፍም ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዥ ፡ በቅርብ ፡ ጊዜ ፡ ስለሚፈጸሙ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ያትታል ። እነዚህም ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ከዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ ጋር ፡ የተዛመዱና ፡ የተዋሃዱ ፡ ናቸው ። ስለዚህ ፡ በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ በወጡት ፡ ሥነ ፡ ሥርዐቶች ፡ መሠረት ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዦች ፡ እንደ ፡ ዓመታዊው ፡ ባጀት ፡ በሕግ ፡ የተደነገጉ ፡ ደንቦች ፡ እንዲሆኑና ፡ እንደሌሎቹ ፡ ሕጎች ፡ መፈጸምና ፡ መጠበቅ ፡ እንደሚገባቸው ፡ ተቆጥረዋል ።

# ምዕራፍ ፡ ፯ ።

## ለዕቅዶችና ፡ ለሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ማከናወኛ ፡ ገንዘብ ፡ ስለ ፡ ማግኘት ።

### ፩/ የባሕር ፡ ማዶ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጮች ።

ለኢትዮጵያ ፡ ልማት ፡ ውጥኖች ፡ የሚሆኑ ፡ የባሕር ፡ ማዶ ፡ የገንዘብ ፡ ምንጮች ፡ በሁለት ፡ ታላላቅ ፡ ክፍሎች ፡ ይከፈላሉ ። እነዚህም ፡ (፩) ለግል ፡ ባለንብረቶችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ (ኮርፖሬሽኖች) የታቀዱ ፡ የልማት ፡ ወጪዎችና ፡ ብድሮች ፡ (፪) ከውጭ ፡ አገር ፡ መንግሥታት ፡ ከኢንተርናሲዮናል ፡ ድርጅቶች ፡ ወይም ፡ ከአንዳንድ ፡ ግላዊ ፡ ድርጅቶች ፡ በመንግሥት ፡ ወይም ፡ በመንግሥት ፡ መሥሪያ ፡ ቤቶች ፡ አማካይነት ፡ የሚገኙ ፡ የገንዘብም ፡ ሆነ ፡ የዕቃ ፡ ብድሮችና ፡ ስጦታዎች ፡ ናቸው ። በቍ. ፶፩/፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም. የውጭ ፡ አገርና ፡ የሀገር ፡ ውስጥ ፡ ገንዘብ ፡ (ካፒታል) በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲውል ፡ ለማበረታታት ፡ የወጣው ፡ ድንጋጌ[38] ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ባለሀብቶችና ፡ አበዳሪ

---

37. እታች ፡ ፫ኛ ፡ ተጨማሪ ፡ ተመልከት ።

38. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፲፮ ፡ ተጠቅሷል ።

ዎች ፡ ገንዘባቸውን ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በልማት ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ እንዲያውሉትና ፡ እንዲሁም ፡ የልማት ፡ ሥራን ፡ ለሚያካሂዱ ፡ ሰዎችና ፡ የንግድ ፡ ማኅበሮች ፡ ብድር፡ እንዲሰጡ ፡ ለማድረግ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኩባንያዎች ፡ የሚያቅዷቸው ፡ ውጥኖች ፡ ከብሔራዊው ፡ ዕቅድ ፡ ጋር ፡ እንዴት፡ አድርገው ፡ እንደሚስማሙ ፡ በሚከተሉት ፡ አንቀጾች ፡ ይብራራል ። ለዕቅዶች ፡ የሚውለው ፡ ገንዘብ ፡ ከሀገር ፡ ውስጥ ፡ ሲገኝና ፡ ከውጭ ፡ አገርም ፡ ሲመጣ ፡ ዕቅዶቹን ፡ ከብሔራዊው ፡ ዕቅድ ፡ ጋር ፡ ለማስማማት ፡ በሚደረገው ፡ ጥረት ፡ የሚያጋጥሙት ፡ ችግሮች ፡ በመሠረታቸው ፡ አንድ ፡ ናቸው ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ገንዘብ ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ በሚውልበት ፡ ጊዜ ፡ ገንዘቡን ፡ በልማት ፡ ላይ ፡ የሚያውሉት ፡ ኩባንያዎች ፡ ሥራቸውን ፡ ከወጡት ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ጋር ፡ እንዲስማሙ ፡ ቢያደርጉ ፡ የልማት ፡ ገንዘብና ፡ ብድር ፡ ከውጭ ፡ አገር ፡ በይበልጥ ፡ ለማግኘት ፡ ይቻላል ። የውጭ ፡ አገር ፡ ኩባንያዎችና ፡ ቅርንጫፎቻቸውም ፡ ልማቶቻቸውንና ፡ ውጥኖቻቸውን ፡ በደረጃ ፡ እየከፈሉ ፡ ከጊዜ ፡ ጊዜ ፡ ከሚወጡት ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ጋር ፡ እንዲስማሙ ፡ ቢያደርጉ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ (ርዳታ) አስተያየት ፡ ሊደረግላቸው ፡ ይቻላል ።

ለመንግሥት ፡ ወይም ፡ ለመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ርዳታ ፡ የሚደረገው ፡ ለተለዩ ፡ ውጥኖች ፡ የሚሆን ፡ ገንዘብ ፡ ለማስገኘት ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያሉትንም ፡ ርዳታዎች ፡ ከዕቅዶችና ፡ ከሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ጋር ፡ መስማማታቸውን ፡ ማረጋገጥ ፡ ከዕቅድ ፡ ማውጣት ፡ ሥራ ፡ አንዱ ፡ ነው ። በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የኢኮኖሚና ፡ የኪነታዊ ፡ (የቴክኒክ) ተራድዖ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡[39] ብቻ ፡ እንደነዚህ ፡ ላሉት ፡ እርዳታዎች ፡ ስምምነት ፡ ለማድረግ ፡ ተገቢ ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ ተገልጿል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ እርዳታ ፡ ከልማት ፡ ውጥኖች ፡ ጋር ፡ በሚገባ ፡ መስማማቱንና ፡ በዕቅዶችና ፡ በሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ውስጥ ፡ የተጠቀሰ ፡ መሆኑን ፡ ማረጋገጥ ፡ የዕቅድ ፡ ክፍል ፡ በተለይም ፡ በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ኀላፊ ፡ የሆነው ፡ ሚኒስትር ፡ ደኤታና ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ኀላፊነት ፡ ነው ። ይህንንም ፡ ከኢኮኖሚና ፡ ከቴክኒካዊ ፡ እርዳታ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ጋር ፡ በመመካከር ፡ ይሠራል ።

በስጦታ ፡ መልክ ፡ የሚገኘው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒክ ፡ ርዳታ ፡ በብድር ፡ እንደሚገኙት ፡ ሀብቶች ፡ ሁሉ ፡ በቍጥር ፡ ሥር ፡ ሆኖ ፡ ከዕቅዶችና ፡ ከሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ጋር ፡ መስማማት ፡ እንደሚገባው ፡ አብዛኛውን ፡ ጊዜ ፡ መገንዘብ ፡ ያዳግታል ። እስከ ፡ አንድ ፡ የተወሰነ ፡ ግምት ፡ ድረስ ፡ ያሉትን ፡ ስጦታዎች ፡ ከቍጥጥር ፡ ውጭ ፡ ማድረግ ፡ ጠቃሚና ፡ ተገቢ ፡ ሆኖ ፡ ቢገኝም ፡ እነዚህ ፡ ስጦታዎች ፡ ከቍጥጥር ፡ ውጭ ፡ የሚሆኑት ፡ ቋሚ ፡ በሆነ ፡ ሕጋዊ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ። ሆኖም ፡ አንዳንድ ፡ ስጦታዎች ፡ ለምሳሌ ፡ የመንገዶች ፡ ማሠሪያ ፡ ገንዘብ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚረዱ ፡ ሰዎች ፡ ወይም ፡ ለብሔራዊ ፡ አየር ፡ መንገድ ፡ የሚሆን ፡ አይሮፕላን ፡ ከብሔራዊው ዕቅድ ፡ ጋር ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ግንኙነት ፡ ስላላቸው ፡ ከዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጋር ፡ በመተባበር ፡ በኢኮኖሚና ፡ ቴክኒካዊ ፡ ተራድዖ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ በጥንቃቄ ፡ መመርመር ፡ ይገባቸዋል ። ያዲስ ፡ መንገድ ፡ ሥራና ፡ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ መቋቋም ፡ በውጭ ፡ አገር ፡ ከሚገኘው ፡ ገንዘብ ፡ ሌላ ፡ ከሀገር ፡ ውስጥም ፡ ተጨማሪ ፡ ገንዘብ ፡ ያስወጣሉ ። ከተሠሩም ፡ በኋላ ፡ ለሥራ ፡ ማካሄጃና ፡ ለጥገና ፡ በየዓመቱ ፡

---

39. እላይ ፡ ምዕራፍ ፡ ፭-(፩) ፡ ተመልከት ።

ተደጋግሞ ፣ የሚመጣ ፣ ወጪ ፣ ያስፈልጋቸዋል ። በስጦታ ፣ መልክ ፣ የሚገኘው ፣ አይሮፕላን ፣ በብሔራዊ ፣ አየር ፣ መንገድ ፣ ውስጥ ፣ ከሚገኙት ፣ አይሮፕላኖች ፣ የተለየ ፣ በመሆኑ ፣ ወይም ፣ ለተፈለገው ፣ አገልግሎት ፣ በጣም ፣ ጠቃሚ ፣ ነው ፣ ከሚባለው ፣ ፍጹም ፣ ልዩ ፣ በመሆን ፣ በጥቂት ፣ ዓመታት ፣ ውስጥ ፣ በአየር ፣ መንገድ ፣ ድርጅት ፣ ላይ ፣ ከጥገናና ፣ ከሥራ ፣ ማካሄጃ ፣ ሌላ ፣ የሌላ ፣ የተሻለ ፣ አይሮፕላን ፣ መግዣ ፣ ያህል ፣ ወጪ ፣ እንደሚያስከትል ፣ አይጠረጠርም ። በፖለቲካ ፣ ረገድ ፣ ከወዳጅ ፣ አገሮች ፣ ስጦታዎችን ፣ አልቀበልም ፤ ማለት ፣ በጣም ፣ አዳጋች ፣ ሲሆን ፣ በኢኮኖሚ ፣ ረገድ ፣ ደግሞ ፣ እንደነዚህ ፣ ያሉትን ፣ ስጦታዎች ፣ መቀበል ፣ አስቸጋሪ ፣ ይሆናል ። እንደዚህ ፣ ያለው ፣ ርምጃ ፣ ሲወሰድ ፣ በኢኮኖሚ ፣ ዕቅድና ፣ በልማት ፣ ሥራ ፣ ላይ ፣ ምን ፣ ሊያስከትል ፣ እንደሚችል ፣ በጥብቅ ፣ መመርመርና ፣ ማጥናት ፣ ያስፈልጋል ።

የውጭ ፣ አገር ፣ መንግሥት ፣ ወይም ፣ የኢንተርናሲዮናል ፣ ድርጅት ፣ ስጦታዎች ፣ በቀጥታ ፣ ለመንግሥት ፣ የሚሰጡ ፣ መሆናቸው ፣ የተለመደና ፣ ተገቢ ፣ ነው ። ሆኖም ፣ እንደዚህ ፣ ያሉት ፣ ስጦታዎች ፣ ሲያጋጥሙ ፣ ለኢኮኖሚና ፣ ቴክኒካዊ ፣ ተራድዖ ፣ ሥራ ፣ መሪ ፣ ጉባኤ ፣ ወዲያውኑ ፣ ማስተላለፍና ፣ ጉባኤው ፣ ከዚያ ፣ ጊዜ ፣ ጀምሮ ፣ አስፈላጊውን ፣ ስምምነት ፣ እንዲዋዋል ፣ ማድረግ ፣ በጣም ፣ ጠቃሚ ፣ ነው ። ይህም ፣ ሲሆን ፣ በዕቅድ ፣ ሥራ ፣ አመራር ፣ የትእዛዝ ፣ ረቂቅ ፣ ውስጥ ፣ እንደተገለጸው ፣ ቦርዱ ፣ ያለመንግሥት ፣ ድርጅቶች ፣ እርዳታ ፣ ምንም ፣ ጠቃሚ ፣ ስምምነት ፣ ለማድረግ ፣ ስለማይችል ፣ የመንግሥት ፣ ድርጅቶችም ፣ በጉዳዩ ፣ መግባታቸው ፣ አይጠረጠርም ። ይህም ፣ በጠቅላላ ፣ ስለ ፣ ውጭ ፣ አገር ፣ እርዳታዎች ፣ ሁሉ ፣ ስምምነት ፣ የማድረግን ፣ ተግባር ፣ ለኢኮኖሚና ፣ ለቴክኒካዊ ፣ ተራድዖ ፣ ሥራ ፣ መሪ ፣ ጉባኤ ፣ መስጠት ፣ ጉባኤው ፣ ሐሳብ ፣ የቀረበባቸውን ፣ ውጥኖች ፣ ጠቅላላ ፣ ሁኔታ ፣ ለመረዳትና ፣ የቀረቡትን ፣ ችሮታዎች ፣ ሁሉ ፣ እያጠቃለለ ፣ ባስፈለገም ፣ ጊዜ ፣ ስጦታው ፣ በሚያመች ፣ አኳኋን ፣ እንዲሆን ፣ ሐሳብ ፣ ለመስጠት ፣ እንዲችል ፣ ያደርገዋል ።

የተፈለገው ፣ ውጥንና ፣ ለወደፊት ፣ የሚያስከትለው ፣ የሀገር ፣ ውስጥ ፣ ገንዘብ ፣ ወጪ ፣ በተፈለገው ፣ ቀጠና ፣ እንዴት ፣ እንደሚውል ፣ የሚያሳየው ፣ የሥራ ፣ ሰንጠረዥ ፣ ወጥቶ ፣ በዕቅድ ፣ ሥራ ፣ ኮሚቴ ፣ ለጊዜው ፣ ከመጽደቁ ፣ በፊት ፣ ከውጭ ፣ አገር ፣ ስለሚገኙ ፣ እርዳታዎች ፣ በውለታ ፣ መልክ ፣ መፈራረም ፣ በቀረበው ፣ የሕግ ፣ ረቂቅ ፣ ውስጥ ፣ ተከልክሏል ። ይህ ፣ በዕቅድ ፣ ሥራ ፣ ጊዜ ፣ አንድ ፣ ቋሚ ፣ ነገር ፣ ለመሥራት ፣ የሚቻልበት ፣ የመዠመሪያው ፣ ደረጃ ፣ ነው ። በዚህ ፣ ጊዜ ፣ እንኳን ፣ እንደዚህ ፣ ያሉ ፣ ውጥኖች ፣ የሚያስከትሉትን ፣ ወጪ ፣ በመገንዘብ ፣ ከውጥኖቹ ፣ ጥቂቶቹ ፣ ይሰረዙ ፣ ይሆናል ። ስለዚህም ፣ ቋሚ ፣ የሆነ ፣ ጥብቅ ፣ ሥነ ፣ ሥርዐት ፣ በማውጣት ፣ መፍትሄ ፣ የማይገኝለትና ፣ የኢኮኖሚና ፣ ቴክኒካዊ ፣ ተራድዖ ፣ ሥራ ፣ መሪ ፣ ጉባኤ ፣ ብቻ ፣ ብልህ ፣ ርምጃ ፣ በመውሰድ ፣ ሊያቃልለው ፣ የሚችል ፣ ችግር ፣ ይፈጠራል ። በውጭ ፣ አገር ፣ ርዳታ ፣ ሊከናወን ፣ የሚችል ፣ ውጥን ፣ በቅደም ፣ ተከተሉ ፣ ተራ ፣ ውስጥ ፣ ዝቅተኛ ፣ ደረጃ ፣ የተሰጠው ፣ እንደ ፣ ሆነ ፣ ሥራ ፣ መሪው ፣ ጉባኤ ፣ ውጥኑ ፣ በልማት ፣ ሥራ ፣ ሰንጠረዥ ፣ ውስጥ ፣ የሚጨምር ፣ መሆኑን ፣ ከማረጋገጡ ፣ በፊት ፣ እንዳችም ፣ የስምምነት ፣ ውል ፣ መፈራረም ፣ የለበትም ።

## ፪/ <u>ግላዊ ፣ የሀገር ፣ ውስጥ ፣ የገንዘብ ፣ ምንጮች ።</u>

የኢትዮጵያ ፣ ብሔራዊ ፣ ባንክ ፣ ከሌሎች ፣ ባንኮች ፣ ጋር ፣ በመመካከር ፣ በየዓመቱ ፣ ለሚቀጥለው ፣ ዓመት ፣ የልማት ፣ ወጪ ፣ በምን ፣ ያህል ፣ መጨመር ፣

እንደሚገባው ፡ እየገመተ ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የሚያቀርበው ፡ ማስታወሻ ፡ ከዕቅድ ፡ ማውጣት ፡ ተግባሮች ፡ አንዱ ፡ ነው ። የዕቅዱ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለጊዜው ፡ ከተስማማበት ፡ በኋላ ፡ የተስማሙበት ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ምን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ለብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ይነገራል ። የኢትዮጵያ ፡ ብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ በሌሎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ በሚገኙ ፡ ባንኮች ፡ ላይ ፡ ቍጥጥር ፡ እንዲያደርግ ፡ በተሰጠው ፡ ሥልጣን ፡ መሠረት ፡ [40] የዓመቱን ፡ የብድር ፡ አሰጣጥ ፡ መመሪያቸውን ፡ (ፖሊሲያቸውን) እንዴት ፡ እንደ ሚያዘጋጁ ፡ መግለጫ ፡ ከመስጠቱም ፡ ሌላ ፡ የራሱም ፡ የቅናሽ ፡ (ዲስካውንት) መመሪያ ፡ ምን ፡ እንደሚሆን ፡ ይገልጽላቸዋል ። [41] እንደዚህ ፡ ያሉትን ፡ መመሪያዎች ፡ ዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዥ ፡ ሕግ ፡ ሆኖ ፡ በታወጁ ፡ ጊዜ ፡ አሻሽሎ ፡ ማውጣት ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆን ፡ ይሆናል ።

መመሪያቸውንና ፡ (ፖሊሲዎቻቸውን) ውጥኖቻቸውን ፡ ከብሔራዊ ፡ የልማት ፡ ዕቅድና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጋር ፡ ካላስማሙ ፡ በስተቀር ፡ የብሔራዊ ፡ ባንክ ፡ ለማንኛውም ፡ ሰው ፡ ኩባንያዎችን ፡ የማቋቋም ፡ መብት ፡ (ሥልጣን) ፡ የአክሲዮኖችን ፡ መጠን ፡ የመጨመርንና ፡ ተስማሚ ፡ የሆነ ፡ ብድር ፡ የማግኘትን ፡ ዕድል ፡ መወሰን ፡ ወይም ፡ መከልከል ፡ አለበት ። የባንክ ፡ ብድር ፡ ለማግኘት ፡ የማይፈልጉ ፡ የአክሲዮኖች ፡ መጠን ፡ እንዲጨመርላቸው ፡ የማይሹ ፡ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ ብድር ፡ የማያስፈልጋቸው ፡ ውጥኖችም ፡ (ፕሮገሮዎች) በቀጥታ ፡ ሳይሆን ፡ በተዘዋዋሪ ፡ መንገድ ፡ ቍጥጥር ፡ ሊደረግባቸው ፡ ይቻላል ። ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ የታክስ ፡ ቅናሽ ፡ በነጻ ፡ ወይም ፡ በርካሽ ፡ የፋብሪካ ፡ ቦታዎችን ፡ የማግኘት ፡ ዕድል ፡ መስጠትና ፡ አንዳንድ ፡ ለጥቅም ፡ የሚውሉ ፡ ዕቃዎችን ፡ በርካሽ ፡ ዋጋ ፡ እንዲያገኙ ፡ የማድረግ ፡ ዘዴ ፡ ተፈላጊ ፡ የሆኑ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማሠራት ፡ ማበረታቻ ፡ ዘዴ ፡ ሊሆን ፡ ይችላል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የታክስ ፡ መጨመር ፡ የወጪና ፡ የገቢ ፡ ዕቃዎች ፡ ጥብቅ ፡ ቍጥጥር ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ምንዛሪን ፡ የመከልከል ፡ ዘዴና ፡ የመሬት ፡ አጠቃቀም ፡ ሁኔታን ፡ በጥብቅ ፡ መቆጣጠር ፡ አንዳንድ ፡ የማይፈለጉ ፡ ሥራዎችን ፡ እንዳይዳብሩ ፡ ለማድረግ ፡ ይጠቅማል ።

## ፫/ <u>ከሕዝብ ፡ የሚገኝ ፡ ገንዘብ</u> ።

የሕዝብ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከወጪ ፡ ቀሪ ፡ ገንዘባቸው ፡ የንግድ ፡ አገልግሎቶችን ፡ በማቋቋም ፡ የሚያስገኙት ፡ ለልማት ፡ የሚውል ፡ ገንዘብ ፡ በነዚሁ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ከሚዘጋጀው ፡ የዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዥ ፡ ረቂቅ ፡ ጋር ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይላካል ። ሆኖም ፡ ለልማት ፡ ጉዳይ ፡ የሚውለው ፡ አብዛኛው ፡ የሕዝብ ፡ ገንዘብ ፡ የሚገኘው ፡ ከዓመታዊው ፡ ባጀት ፡ ነው ። የዓመታዊውም ፡ ባጀት ፡ እንዴት ፡ እንደሚዘጋጅና ፡ እንደሚቀርብ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ ይብራራል ።

የዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለጊዜው ፡ የጸደቀ ፡ መሆኑን ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ሲረዱ ፡ የድርጅቶች ፡ የልማት ፡ ክፍሎች ፡ ለጸደቁት ፡ ውጥኖች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ባጀት ፡ ለመገመትና ፡ ለማዘጋጀት ፡ ጉዳዩ ፡ ከሚጠቅሳቸው ፡ ክፍሎች ፡ ጋር ፡ በኅብረት ፡ ይሠራሉ ። የእያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ዋጋ ፡

---

40. ስለ ፡ ገንዘብና ፡ ስለ ፡ ባንክ ፡ በ፲፱፻፶፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ አላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ፡ የተጠቀሰው ፡ አዋጅ ፤ ቍጥር ፡ ፪ ።

41. የባንክ ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ ጊዜው ፡ ሁናቴ ፡ ተለዋዋጭ ፡ እንዲሆን ፤ መሻሻል ፡ ሳያስፈልገው ፡ አይቀርም ።

ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዕቅዱ ፡ ሥራ ፡ ዝግጅት ፡ ላይ ፡ ተጣርቶ ፡ ስለሚቆይ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ በቶሎ ፡ መፈጸም ፡ ይገባዋል ። እያንዳንዱም ፡ ክፍል ፡ (ወረቱንና) ገንዘቡን ፡ (ካፒታሉንና) እየተደጋገመ ፡ የሚመጣውን ፡ ወጪ ፡ አጠቃልሎ ፡ ባጀቱን ፡ ለገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ያቀርባል ። የአስተባባሪና ፡ የሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ድርጅት ፡ ሰንጠረዥ ፡ ሲያዘጋጅ ፡ እንዲጠቀምበት ፡ (ወረቱን) ፡ ገንዘቡን ፡ (ካፒታል) የሚያሳየው ፡ ቅጅ ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ይላካል ።

የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ግዛት ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ ያዘጋጃል ።[42] ተደጋግሞ ፡ የሚመጣውን ፡ ወጪ ፡ ለመገመት ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከእንያንዳንዱ ፡ ሚኒስቴር ፡ የሚቀርብለትን ፡ ሐሳብ፡ ይመለከታል ።[43] ነገር ፡ ግን ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ የሚያቀርበው ፡ የራሱን ፡ አስተያየት ፡ ነው ። ሆኖም ፡ ልማት ፡ ጠቀስ ፡ በሆነው ፡ ወጪ ፡ ሁሉ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የጸደቀ ፡ ስለሚሆንና ፡ ሚኒስትሩም ፡ የዚሁ ፡ ጉባኤ ፡ አባል ፡ ስለሆነ ፡ በዚህ ፡ ረገድ ፡ ያለውን ፡ ባጀት ፡ ጠልቆ ፡ ለብቻው ፡ መመርመር ፡ አያስፈልገውም ። ይሁን ፡ እንጂ ፡ የመንግሥት ፡ ገቢ ፡ ገንዘብንና ፡ ሌሎችንም ፡ ጠቅላላውን ፡ ባጀት ፡ ለማስተካከል ፡ የሚረዱትን ፡ ዘዴዎች ፡ ማግኘት ፡ ከተግባሮቹ ፡ አንዱ ፡ ክፍል ፡ ነው ። ጠቅላላውም ፡ ባጀት ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ በባጀት ፡ ዓመት ፡ መዠመሪያና ፡ በዓመቱም ፡ ውስጥ ፡ ይደርሳል ፡ ተብሎ ፡ በተገመተው ፡ በሀገሪቱ ፡ ኢኮኖሚና ፡ የገንዘብ ፡ ሁኔታዎች ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ አለበት ። ባጀቱ ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ጊዜ ፡ የነዚህን ፡ ሁኔታ ፡ መገመት ፡ ስለሚቻል ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የልማት ፡ ወጪ ፡ ባጀት ፡ እንዲቀነስ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አስፈላጊ ፡ ይሆንበት ፡ ይሆናል ። እንደዚህ ፡ ከሆነ ፡ ሚኒስትሩ ፡ በቅደም ፡ ተከተል ፡ ደረጃ ፡ ዝቅተኛ ፡ ቦታ ፡ የያዙት ፡ የልማት ፡ ውጥኖች ፡ እንዲሠረዙ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አለበት ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልማት ፡ ባጀትን ፡ ለመቀነስ ፡ ምንም ፡ ሌላ ፡ ሐሳብ ፡ ማቅረብ ፡ አያስፈልግም ።

የሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ባጀት ፡ የሚፈቀድበትን ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ ሲያዘጋጅ ፡ እንዲረዱበት ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያወጣውን ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ የራሱን ፡ አስተያየትና ፡ ሐሳብ ፡ ጨምሮ ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ያቀርባል ።[44] ተደጋግሞ ፡ የሚመጣውን ፡ ባጀት ፡ በሚኒስትሮች ፡ አስተያየት ፡ መቀነስ ፡ ሲቻል ፡ የልማት ፡ ባጀት ፡ መቀነስ ፡ የሚቻለው ፡ የዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ላይ ፡ ዝቅተኛ ፡ ደረጃ ፡ ያላቸውን ፡ ፕሮዤዎች ፡ በመሠረዝ ፡ ብቻ ፡ ነው ። የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ባወውጣ ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ደረጃ ፡ ባይስማሙ ፡ እንደገና ፡ እንዲያጠናው ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ መመለስ ፡ ተገቢ ፡ ነው ።

በየአንዳንዱ ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ለተጠቀሱት ፡ ለውጥኖች ፡ የሚያስፈልገውን ፡ ገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ በሁለት ፡ ወይም ፡ በበለጡ ፡ ዓመታት ፡ ውስጥ ፡ ማድረግ ፡ እንደሚቻልና ፡ የነዚህም ፡ ዓመታት ፡ ባጀት ፡ ወደ ፡ ፓርላማ ፡ ሲላክ ፡ ውጥኖቹን ፡ በነዚህ ፡ ዓመቶች ፡ ባጀት ፡ ውስጥ ፡ ለማጠቃለል ፡ መቻሉን ፡ የብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ ይገልጻል ። በሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ውስጥ ፡ ደግሞ ፡ እያንዳንዱ ፡ ሚኒስትርና ፡ እያንዳንዱ ፡ የመን

---

42. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍ ፡ 6 ፡ የተጠቀሰው ፡ ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ በ፲፱፻፷፮ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ አዋጅ ፡ ቍ ፡ ፵፯ ፡ (ሀ) ።

43. እላይ ፡ የተጠቀሰው ፡ አዋጅ ፡ ቍጥር ፡ ፲፯ ።

44. ተሻሽሎ ፡ የወጣው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ አንቀጽ ፡ ፻፲፩ ።

ግሥት ፡ ድርጅት ፡ ሹም ፡ በተያዘው ፡ የባጀት ፡ ዓመት ፡ ውስጥ ፡ ለማይጀመሩ ፡ ውጥኖች ፡ የተመደበለትን ፡ ገንዘብ ፡ ለሌሎች ፡ የልማት ፡ ውጥኖች ፡ ለማዋል ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሆኑ ፡ በልማት ፡ ባጀቱ ፡ ውስጥ ፡ መገለጽ ፡ ይገባዋል ፡ ይላል። ስለሆነም ፡ እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ለክፍሉ ፡ ከተመደበለት ፡ ጠቅላላ ፡ ገንዘብ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ መብለጥ ፡ የለበትም ። በተጨማሪም ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ በቅድሚያ ፡ በሐሳቡ ፡ መስማማት ፡ እንዳለበት ፡ ተገልጿል ። እንደነዚህ ፡ ያሉት ፡ አንቀጾች ፡ የታቀዱት ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ (በኢኮኖሚና) በቍጠባና ፡ በሚገባ ፡ እንዲፈጸሙ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ መስማማት ፡ የሚፈለገው ፡ ወጪ ፡ የተደረገው ፡ ገንዘብ ፡ ያለአግባብ ፡ እንዳይባክን ፡ (እንዳይሰረቅ) ለመቆጣጠር ፡ ነው ። በተጨማሪም ፡ የሚኒስትሩ ፡ መስማማት ፡ ውጥኖችን ፡ ጠቃሚነት ፡ ለመገመትና ፡ በመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ ዕቅዶች ፡ ውስጥ ፡ መጨመራቸውን ፡ ለማረጋገጥ ፡ ይረዳዋል ። ደግሞም ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከጠቅላላው ፡ ባጀት ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ የማይበልጠውን ፡ ገንዘብ ፡ ለሌሎች ፡ ውጥኖች ፡ ሲያውል ፡ ተደጋግመው ፡ በሚመጡት ፡ ባጀቶች ፡ ላይ ፡ አስፈላጊ ፡ ለውጥ ፡ ማድረግ ፡ ማስፈለጉን ፡ ይገነዘበው ፡ ይሆናል ። የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ያልተስማማ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወይም ፡ የታሰበው ፡ ባጀት ፡ ከጠቅላላው ፡ የልማት ፡ ባጀት ፡ ከአሥራ፡ አምስት ፡ በመቶ ፡ የበለጠ ፡ እንደሆነ ፡ የልማቱ ፡ ሥራ ፡ የሚጠቅሰው ፡ ሚኒስቴር ፡ ሌላ ፡ ተጨማሪ ፡ ባጀት ፡ እንዲሰጠው ፡ ለመጠየቅ ፡ ይችላል ። [45]

## ፬/ የጠቅላላ ፡ የልማት ፡ ገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ።

የኢኮኖሚ ፡ ዕቅድ ፡ ችግር ፡ ዋና ፡ መፍትሔ ፡ የታቀዱት ፡ ውጥኖች ፡ ሊገኝ ፡ በሚችለው ፡ ገንዘብ ፡ ልክ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማድረግና ፡ በተወሰነው ፡ ገንዘብ ፡ በሙሉ ፡ መጠቀም ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዡን ፡ ለማጽደቅ ፡ እንዲችል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ገንዘብ ፡ እንዳለ ፡ ግምቱን ፡ ማወቅ ይኖርበታል ። አሁን ፡ እንደሚሠራው ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ የሱን ፡ የተጠቃለለ ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ እስኪያቀርብ ፡ ድረስ ፡ ያለው ፡ ገንዘብ ፡ ግምት ፡ አይታወቅም ። በዚህም ፡ ምክንያት ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በተገቢው ፡ ጊዜ ፡ ውሳኔ ፡ ሊሰጥ ፡ አይችልም ። ስለዚህ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ለልማት ፡ ሥራዎች ፡ የሚወጣውን ፡ ገንዘብ ፡ የመዠመሪያ ፡ ግምት ፡ አስቀድሞ ፡ አዘጋጅቶ ፡ ለዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ መስጠት ፡ ይኖርበታል ። የኢኮኖሚና ፡ የቴክኒካዊ ፡ ተራድዖ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ያደረገው ፡ የውጭ ፡ አገር ፡ ርዳታ ፡ ስምምነትም ፡ ከዚህ ፡ ግምት ፡ ጋር ፡ አብሮ ፡ መቅረብ ፡ ይገባዋል ። በዚህ ፡ መንገድ ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከተዘጋጀው ፡ ዓመታዊ ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ ጋር ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ የሚቀርብ ፡ አንድ ፡ የተስተባበረ ፡ ዓመታዊ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ለማዘጋጀት ፡ ይቻላል ።

በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የአስተባባሪና ፡ የአስፈጻሚ ፡ ድርጅት ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ በኩል ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በሚላከው ፡ በዓመታዊ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ረቂቅ ፡ ውስጥ ፡ የተጠቃለለ ፡ አንድ ፡ የልማት ፡ ገቢና ፡ ወጪ ፡ ግምት ፡ ያዘጋጃል ።

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤም ፡ ይህንን ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ መርምሮ ፡ ያጸድቀዋል ። ይህንንም ፡ ሲያደርግ ፡ በቅድሚያ ፡ ተስማምተውበት ፡ ከነበረው ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ አሁን ፡ የተተውትን ፡ ውጥኖች ፡ እንደገና ፡ ይመ

---

45. እላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ ቍጥር ፡ ፻፲፰ ።

ረምር ፡ ይሆናል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዕቅድ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ የሚደረገው ፡ ማንኛውም ፡ ለውጥ ፡ በቅድሚያ ፡ በተሰጠው ፡ ቅደም ፡ ተከተል ፡ ደረጃ ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ ይገባዋል ።

የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ያጸደቀው ፡ ዓመታዊው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ እያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ገንዘብ ፡ እንደሚያገኝ ፡ ከሚያሳየው ፡ መግለጫ ፡ ጋር ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ጉባኤ ፡ ይቀርባል ። ይህም ፡ በገንዘብ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ከተዘጋጀው ፡ ከዓመታዊው ፡ የባጀት ፡ ግምት ፡ ጋር ፡ ለሚኒስትሮች ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ይቀርብና ፡ ሁለቱም ፡ አንድነት ፡ ይመረመራሉ ። ከተስማሙበትም ፡ በኋላ ፡ ለድንጋጌ ፡ ወደ ፡ ፓርለማ ፡ ይላክና ፡ ከዚያም ፡ የመጨረሻ ፡ ውሳኔ ፡ እንዲያደርጉና ፡ እንዲያውጁት ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይቀርባል ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

## አፈጻጸም ፡ ቊጥጥርና ፡ ምርመራ ።

### ፩/ የአፈጻጸም ፡ ዘዴዎች ።

የኢኮኖሚና ፡ የማኅበራዊ ፡ ኑሮ ፡ ዕቅዶችን ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦችንና ፡ ውጥኖችን ፡ ተከታትሎ ፡ የማስፈጸም ፡ ሥልጣን ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ መስጠት ፡ አለበት ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሥልጣን ፡ በነዚሁ ፡ ድርጅቶች ፡ ሥልጣንና ፡ ተግባሮች ፡ ውስጥ ፡ ስለሚጠቀለል ፡ በሕግና ፡ በተለምዶ ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ ምንም ፡ ለውጥ ፡ አያስከትልም ።

ለዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሥልጣን ፡ ሲሰጥ ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ድርጅቶችና ፡ በዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ መካከል ፡ ተጨማሪ ፡ መተባበርና ፡ ጥብቅ ግንኙነት ፡ እንዲኖር ፡ ያስፈልጋል ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ስለሌላቸው ፡ በቴክኒካዊና ፡ በአስተዳደር ፡ ሥራ ፡ በኩል ፡ አንዱ ፡ ዓይነት ፡ ነገር ፡ በሁለቱም ፡ በኩል ፡ ሊሠራ ፡ ስለሚቻል ፡ ያንዱ ፡ ሥራ ፡ ከሌላው ፡ ጋር ፡ ስለሚጋጭና ፡ ስለ ፡ ኀላፊነት ፡ አለመግባባት ፡ ስለሚፈጠር ፡ ሥራው ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ ይጎተታል ። በተጨማሪም ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ፡ በየቀኑ ፡ የፕሮግራሞችን ፡ ሥራ ፡ ለማስፈጸም ፡ ሲጣጣሩ ፡ ዕቅዶችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ አይመቻቸው ፡ ይሆናል ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ አሁን ፡ ያሉትን ፡ ለወደፊት ፡ ከሚታቀዱት ፡ ጋር ፡ ተመሳሳይ ፡ የሆኑትን ፡ ውጥኖች ፡ በዚያው ፡ መሥመር ፡ ለማካሄድ ፡ ኀላፊ ፡ ናቸው ፤ ያሉት ፡ ውጥኖችና ፡ ያሁኑ ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ዘዴ ፡ በሚገባ ፡ አይካሄዱም ፤ የሚለው ፡ ነቀፌታ ፡ ድርጅቶች ፡ ለማቋቋም ፡ ወይም፡ ካሉት ፡ ድርጅቶች ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ፡ ለመውሰድ ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ አይሆንም ። ግን ፡ ያሁኑን ፡ አቋምና ፡ ያለውን ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ለማሻሻል ፡ በቂ ፡ ምክንያት ፡ ነው ። አዳዲስ ፡ ወይም ፡ ሌሎች ፡ አስፈጻሚ ፡ ድርጅቶችን ፡ ለማቋቋም ፡ የሚያስፈልገው ፡ ሥራው ፡ በዝቶ ፡ አሁን ፡ ያሉት ፡ ድርጅቶች ፡ ደህና ፡ አድርገው ፡ ለማካሄድ ፡ ከሚችሉበት ፡ የመጨረሻ ፡ ደረጃ ፡ ቢያልፍ ፡ ነበር ። ሆኖም ፡ ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ይህን ፡ የሚያሳይ ፡ ምንም ፡ ማስረጃ ፡ የለም ።

### ፪/ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ቊጥጥር ።

የራሳቸውን ፡ ድርጅቶች ፡ ጠቀስ ፡ ከሆኑት ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ በተላመዱትና ፡ ለማስፈጸም ፡ የሚረዳውን ፡ የሀብት ፡ ምንጭ ፡ በደንብ ፡ በሚያ

ውቁት ፣ በልማት ፡ ክፍሎች ፡ በደንብ ፡ በመጠቀምና ፡ እንዲሁም ፡ ዕቅድ ፡ በሚ ወጣበት ፡ ጊዜ ፡ እንዲሳተፉ ፡ በማድረግ ፡ የድርጅቶች ፡ ኀላፊነት ፡ ሊጠነክርና ፡ ሥራው ፡ ሊፋጠን ፡ ይችላል ።

በዓመታዊው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ እያንዳንዱ ፡ ውጥን ፡ ለመቆጣጠርና ፡ ተከታትሎ ፡ ለማስፈጸም ፣ እንዲያመች ፡ በአንድ ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅት ፡ ሥር ፡ ይሆናል ። ከነዚህም ፡ ድርጅቶች ፡ ተግባር ፡ አንዱ ፡ ለአንድ ፡ ለተወሰነ ፡ ውጥን ፡ ኀላፊ ፡ የሆነው ፡ ዝቅተኛ ፡ ወኪል ፡ ወይም ፡ ተዋዋይ ፡ (ተቋራጭ) የተደረገውን ፡ ርምጃና ፡ በሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ውስጥ ፡ ያልታየ ፡ መዘ ግየት ፡ ቢፈጠር ፡ የሆነበትን ፡ ምክንያት ፡ በተጨማሪም ፡ የገንዘብ ፡ አወጣጥ ፡ ሁኔታን ፡ የሚያመለክት ፡ ሪፖርት ፡ በሦስት ፡ በሦስት ፡ ወር ፡ ማዘጋጀቱን ፡ መቆ ጣጠር ፡ ይሆናል ። የልማት ፡ ክፍሎችም ፡ እነዚህን ፡ ሪፖርቶች ፡ ተመልክተው ፡ ውጥኖቹን ፡ ለመፈጸም ፡ የሚያግዱትን ፡ እክሎች ፡ ለማስወገድ ፡ የሚቻልበትን ፡ ዘዴ ፡ አዘጋጅተው ፡ ያቀርባሉ ። ሆኖም ፡ ማንኛውም ፡ ለውጥ ፡ በብሔራዊ ፡ የዕ ቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ትእዛዝ ፡ ውስጥ ፡ በተገለጸው ፡ በገንዘብ ፡ ሁኔታ ፡ መጠን ፡ መሠረት ፡ መሆን ፡ አለበት ።

የልማት ፡ ጣቢያው ፡ የማሻሻያ ፡ ሐሳቦችና ፡ የተስተባበሩት ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ ሪፖርቶች ፣ ለጥናት ፡ ለተገቢው ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ እንዲሁም ፡ ሪፖር ቶችን ፡ ሲያዘጋጁና ፡ ሲያጠኑ ፡ እንዲረዱበት ፡ ለቀጠናው ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አስ ፈጻሚ ፡ ኮሚቴ ፡ ይላካሉ ።

ተከታትሎ ፡ ስለማስፈጸም ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ የሚያቀርቡአቸውን ፡ ሪፖርቶች ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚገኘው ፡ ተገቢው ፡ የቀጠና ፡ ክፍል ፡ ያጠናና ፡ ምን ፡ ዓይነት ፡ እርምጃ ፡ መውሰድ ፡ እንደሚያስፈልግ ፡ ሐሳብ ፡ ያቀርባል ። እነዚህንም ፡ የቀረቡትን ፡ ሐሳቦች ፡ የአስተባባሪና ፡ አስፈጻሚ ፡ ድር ጅት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ያስተባብራቸውና ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስ ኪያጅ ፡ በኩል ፣ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤና ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ኮሚቴ ፡ ይቀርባሉ ።

ትእዛዝ ፡ ቍ. ፩ ፡ በሚሰጠው ፡ ሥልጣን ፡[46] መሠረት ፡ የዕቅድ፡ሕግ ፡ በደንብ፡ መፈጸሙንና ፣ የወጡት ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ በሚገባ ፡ መካሄዳቸ ውን ፡ ለመቆጣጠር ፡ ኀላፊ ፡ ስለሆነ ፡ ከላይ ፡ የተጠቀሱት ፡ ሪፖርቶች ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩም ፡ መላክ ፡ አለባቸው ። የጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በዕ ቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ የቀረቡትን ፡ ሐሳቦች ፡ መርምሮ ፡ ከተስማማባቸው ፡ በኋላ ፣ ለሚጠቅሳቸው ፡ የመንግሥት ፡ ድርጅቶች ፡ ያስተላልፋል ፤ በተጨማሪም ፡ ጉድለቶችን ፡ ለማረምና ፡ የተስማሙባቸውን ፡ ሐሳቦች ፡ ለማካሄድ ፡ የተወሰደውን ፡ ርምጃ ፡ የሚጠቅስ ፡ መረጃ ፡ ይሰበስባል ። ሕግና ፡ የሥነ ፡ ሥርዓት ፡ መመሪያዎች ፡ የሚረዱት ፣ እንደነዚህ ፡ ያሉ ፡ ቍጥጥሮች ፡ ለማድረግ ፡ የሚጠቅሙ ፡ መረጃዎች ፡ ለመሰብሰብ ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ ሌላም ፡ ጠንከር ፡ ያለ ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ ርምጃ ፡ መው ሰድ ፡ ያሻል ።

ለማንኛውም ፡ የኢኮኖሚ ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አፈጻጸም ፤ ሥራ ፡ ማመዛዘን ፡ በጣም ፡ ጠቃሚ ፡ ነው ። የሥራ ፡ ማመዛዘን ፡ ከሌለ ፡ ውጥኖች ፡ በተቃና ፡ መን

---

46. እላይ ፡ በግርጌ ፡ ማስረጃ ፡ ቍጥር ፡ 6 ፡ የተጠቀሰው ፤ በትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፪ ፡ ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ፣ ፫ኛ ፣ ዓመት ፡ ቍጥር ፡ ፩ ፡ የተሻሻለው ፡ ስለ ፡ ሚኒስትሮች ፡ ሥልጣንና ፡ ሥራ ፡ በ፲፱፻፴፭ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የወጣው ፡ ትእዛዝ ፡ ቍጥር ፡ ፵፮—ሀ ።

ገድ ፡ አይካሄዱም ፤ የዕቅድ ፡ ክፍሎችም ፡ የታቀዱትን ፡ እውነተኛ ፡ ግቦች ፡ ይዘንጓቸዋል ። የሥራ ፡ ማመዛዘን ፡ ተግባር ፡ የሚጀመረው ፡ የሦስት ፡ ወር ፡ የሥራ ፡ ርምጃ ፡ ሪፖርት ፡ በበታች ፡ ወኪሎችና ፡ በተዋዋዮች ፡ (ተቋራጮች) ሲሰጥ ፡ ነው ። በየአንዳንዱም ፡ ዓመት ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፡ እያንዳንዱ ፡ የቀጠና ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ በነዚህ ፡ ሪፖርቶችና ፡ ራሱ ፡ ባገኘው ፡ መረጃ ፡ በመጠቀም ፡ ለራሱ ቀጠና ፡ የሚሆን ፡ የማመዛዘኛ ፡ ሪፖርት ፡ ያዘጋጃል ። እንደዚህ ፡ ያለው ፡ ሪፖርት ፡ ያለፈውን ፡ ዓመት ፡ የቀጠናውና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ጥናትና ፡ የተገኙትንም ፡ ጉድለቶች ፡ እንዲሁም ፡ የሚሻሻሉበትን ፡ ዘዴዎች ፡ ይጠቀልላል ።

እያንዳንዱም ፡ የቀጠና ፡ ክፍል ፡ የተገቢውን ፡ የቀጠና ፡ ልማት ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሪፖርት ፡ ያጠናና ፡ ስለ ፡ ቀጠናው ፡ የራሱን ፡ ሪፖርት ፡ ያዘጋጃል ። ይህም ፡ ሪፖርት ፡ በሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ሪፖርት ፡ በዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ክፍሎች ፡ በተሰበሰቡት ፡ መረጃዎችና ፡ በጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዥው ፡ አስተያየቶች ፡ ላይ ፡ መመሥረት ፡ አለበት ። የየቀጠናው ፡ ክፍል ፡ ሪፖርቶች ፡ ግልጽ ፡ ያሉና ፡ እውነተኛ ፡ (ትክክል) መሆን ፡ ይገባቸዋል ። የመጨረሻው ፡ ሪፖርት ፡ ለሕዝብ ፡ የሚቀርብ ፡ መሆን ፡ አይገባውም ። ስለዚህ ፡ አዘጋጂዎቹ ፡ የሚመስላቸውን ፡ ነቀፌታ ፡ ሁሉ ፡ በሪፖርቱ ፡ ላይ ፡ ለማስፈር ፡ ምንም ፡ መፍራት ፡ የለባቸውም ። ነቀፌታ ፡ ከማቅረብና ፡ ጥልቅ ፡ ጥናት ፡ ከማድረግ ፡ ሌላ ፡ ሪፖርቱ ፡ የያንዳንዱን ፡ ውጥን ፡ ለብሔራዊ ፡ ለክፍለ ፡ ሀገሩና ፡ (ሪጅናል) ለየቀጠናው ፡ ኢኮኖሚ ፡ ያለውን፡ ጠቃሚነት ፡ እንዲሁም ፡ እንዴት ፡ አድርጎ ፡ የየቀጠናው ፡ ሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ከረዥም ፡ ዘመን ፡ ዕቅዶች ፡ ጋር ፡ እንደሚዛመድ ፡ ማሳየት ፡ አለበት ።

የአስተባባሪና ፡ አስፈጻሚ ፡ ድርጅት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ የቀጠና ፡ ክፍሎችን ፡ ሪፖርቶች ፡ እያስተባበረ ፡ የራሱንም ፡ አስተያየት ፡ ይሰጣል ። የዚህም ፡ ውጤት ፡ የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ዓመታዊ ፡ ሪፖርት ፡ ይሆናል ። የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ለዕቅድ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤና ፡ ለጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሪፖርቱን ፡ ያቀርባል ።

## ፫/ <u>የዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ምርመራ</u> ።

የረዥም ፡ ዘመን ፡ ውጥኖች ፡ ዕቅዶችንና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረገዦችን ፡ ለማዘጋጀት ፡ መነሻ ፡ መሠረት ፡ ናቸው ። እነዚሁም ፡ በሕግ ፡ በኩልም ፡ ሆነ ፡ በፖለቲካ ፡ ረገድ ፡ በፓርለማም ፡ ሆነ ፡ በሌላ ፡ በኩል ፡ መጽደቅ ፡ ሳያስፈልጋቸው ፡ ሊሠራባቸው ፡ ይቻላል ። ስለዚህ ፡ የነዚህ ፡ ውጥኖች ፡ ምርመራ ፡ ምንም ፡ እንኳን ፡ እንደ ፡ ቀላል ፡ ነገር ፡ ባይወሰድ ፡ አንዳችም ፡ ሕጋዊ ፡ ፖለቲካዊ ፡ ወይም ፡ የአስተዳደር ፡ ችግሮችን ፡ አያስከትልም ።

በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የአምስት ፡ ዓመቱ ፡ ዕቅድ ፡ ሥነ ፡ ሥርዓትን ፡ በተከተለ ፡ መንገድ ፡ ለዕቅድ ፡ ሥራ ፡ መሪ ፡ ጉባኤ ፡ ቀርቦ ፡ ተነጋግረውበት ፡ ከጸደቀ ፡ በኋላ ፡ በዚሁ ፡ ረገድ ፡ በጽሑፍ ፡ ታትሞ ፡ ይወጣል ። ምንም ፡ እንኳን ፡ በሕግ ፡ ተደንግጎ ፡ ባይወጣ ፡ ይህ ፡ ዕቅድ ፡ ትልቅ ፡ ክብር ፡ ያለው ፡ ፖለቲካ ፡ ነክ ፡ መዝገብ ፡ ነው ፤ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የሚለዋወጥ ፡ ከሆነም ፡ ማንኛውንም ፡ የዕቅድ ፡ ተግባር ፡ ያቃውሳል ። በዕቅዱ ፡ መሠረት ፡ የአፈጻጸሙን ፡ ዘዴ ፡ መለዋወጥ ፡ የተለመደ ፡ ሲሆን ፡ ሳለ ፤ በዕቅዱ ፡ ውስጥ ፡ የተዘረዘሩትን ፡ ሁሉ ፡ በተቻለ ፡ መጠን ፡ እንዳይለዋወጡ ፡ ማድረግ ፡ ያስፈልጋል ። በሌላ ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የአፈጻጸሙ ፡ ዘዴ ፡ ተበላሽቶ ፡ ሳለ ፡ በወረቀት ፡ ላይ ፡ ባለው ፡ ዕቅድ ፡ ላይ ፡ እምነትን ፡ መጣል ፡ በጣም


ስህተት ፡ ነው ። እንደዚህ ፡ ያለ ፡ ሁኔታ ፡ ሲፈጠር ፡ ዕቅዱ ፡ እንደ ፡ ገና ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ በሚገባ ፡ አኳኋን ፡ በሥነ ፡ ሥርዓት ፡ ተጠንቶ ፡ ተሻሽሎና ፡ ጸድቆ ፡ ታትሞ ፡ መውጣት ፡ አለበት ።

ባሁኑ ፡ ጊዜ ፡ ዓመታዊ ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ሰንጠረዦች ፡ ተጠንተው ፡ የሚጸድቁት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ዕቅድ ፡ ነው ፤ እነዚሁም ፡ ሕጋዊነት ፡ የሌላቸው ፡ የፖለቲካ ፡ መዝገቦች ፡ ናቸው ። ሆኖም ፡ ለወደፊት ፡ እንደዚህ ፡ ያሉት ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ልክ ፡ እንደሌላው ፡ ዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ በፓርለማ ፡ ተደንግገው ፡ ሕጋዊ ፡ መዝገቦች ፡ እንዲሆኑ ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቧል ። እነዚህም ፡ ሊታረሙ ፡ የሚችሉት ፡ የብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ማረሚያ ፡ ሕግ ፡ ብቻ ፡ መሆን ፡ አለበት ። የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ የሚዘጋጁት ፡ ልክ ፡ እንደ ፡ ዓመታዊ ፡ ባጀት ፡ ላንድ ፡ ዓመት ፡ ብቻ ፡ ስለሆነ ፡ በጥንቃቄ ፡ ከተሠሩ ፡ እምብዛም ፡ ለውጥ ፡ እያስፈልጋቸውም ። ለውጥ ፡ አስፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ ከተገኘም ፡ ተጨማሪ ፡ ባጀት ፡ ማስፈለጉ ፡ አይቀርምና ፤ ባጀቱ ፡ ከተሻሻለው ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዥ ፡ ጋር ፡ መስተባበር ፡ አለበት ።

ባሉት ፡ ዕቅዶችና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ውስጥ ፡ የተጠቃለሉት ፡ ውጥኖች ፡ የሥራ ፡ አፈጻጸም ፡ ለውጥ ፡ ባስፈለገው ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አጥኚ ፡ ጉባኤ ፡ ከተስማማበት ፡ በኋላ ፡ በሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ። በብሔራዊ ፡ የዕቅድ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ የትእዛዝ ፡ ረቂቅ ፡ መሠረት ፡ ለውጥ ፡ ሊደረግላቸው ፡ ለማይችሉ ፡ ጉዳዮች ፡ የመጀመሪያዎቹ ፡ ዕቅዶች ፡ ወይም ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦች ፡ ሲሠሩ ፡ በተወሰዱት ፡ ሥነ ፡ ሥርዓቶች ፡ መሠረት ፡ አስፈላጊው ፡ ለውጥ ፡ መደረግ ፡ አለበት ። ዕቅዶችንና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦችን ፡ የማካሄድ ፡ ልምድ ፡ እየዳበረ ፡ ሲሄድ ፡ ዕቅዶችንና ፡ የሥራ ፡ ሰንጠረዦችን ፡ የመመርመርን ፡ ሥልጣን ፡ በዕቅድ ፡ ሥራ ፡ ደረጃ ፡ ዝቅተኛ ፡ ለሆኑት ፡ ክፍሎች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ለሥራ ፡ አስፈጻሚ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ መስጠት ፡ ይቻል ፡ ይሆናል ። ሆኖም ፡ በዚህ ፡ አኳኋን ፡ የተሰጠ ፡ ሥልጣን ፡ በወጣው ፡ ሕግ ፡ መሠረትና ፡ በጥብቅ ፡ ቍጥጥር ፡ ሥር ፡ መፈጸም ፡ አለበት ።


፩ኛ ፡ ተጨማሪ ።

## በጠቅላይ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሥር ፡ ያሉ ፡ የዕቅድ ፡ ክፍሎች ።



፪ኛ ፡ ተጨማሪ ፡

## የዕቅድ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ አቋም ።



## ዕቅድን ፡ የሥራ ፡ ሠንጠረዥና ፡ በጀትን ፡ እንዴት ፡ ማስተባበርና ፡ ማጽደቅ ፡ እንደሚቻል ፡ የቀረበ ፡ ሐሳብ ።
## (የን. ነ. የዕቅድ ፡ ቦርድ ፡ እንዳለ ፡ እንደሚቆይ ፡ በመገመት ፡ የተዘጋጀ) ።

